ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
MINISTRY OF INDUSTRY

# ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር



# የአምራች ኢንዱስትሪ የአቅም ልማት ስትራቴጂ የማስተግበሪያ ዕቅድ

(ከ2016-2018ዓ.ም)

አዲስ አበባ

2016 ዓ.ም

# ይዘት


መግቢያ ........................................ 2
1. የአቅም ልማት ስትራቴጂ አጭር መግለጫ (Overview) ........ 3
2. የስትራቴጂው የትግበራ ማዕቀፍ (framework) ........ 5
2.1. ርዕይ ተልዕኮና እሴቶች ........ 5
2.2. የስትራተጂው ወሰን፣ መርሆዎችና ታሳቢዎች ........ 6
2.2.1. የስትራቴጂ ዕቅዱ ወሰን ........ 6
2.2.2. መርሆዎች ........ 6
2.2.3. የዕቅዱ ታሳቢዎች ........ 6
2.3. ዓላማዎችና በመካከለኛ ዘመን የሚጠበቅ ውጤት ........ 7
2.3.1. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች አቅም ልማት የተቀመጡ ዓላማዎች ........ 7
2.3.2. በመካከለኛ ዘመን የሚጠበቅ ውጤት ........ 8
2.4. የትኩረት መስኮችና ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች ........ 9
2.4.1. ተቋማዊ አቅም ልማት ........ 9
2.4.2. የፋይናንስና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የመጠቀም አቅም ማሳደግ ........ 9
2.4.3. የአምራች ኢንዱስትሪ የአቅም ልማት ስልጠና ........ 10
2.4.4. የጥናትና ምርምር አቅምን ማሳደግ ........ 11
2.4.5. የአምራች ኢንዱስትሪውን እና የዘርፉ አስፈጻሚ አካላትን በዘላቂነት ማብቃት ........ 11
2.5. ስትራቴጂያዊ ግብ፣ የቁልፍ ውጤት አመላካቶችና ዝርዝር ተግባራት ........ 12
2.5.1. የአምራች የአቅም ልማት ስትራቴጂ የመካከለኛ ዘመን የትግበራ የድርጊት መርሃ ግብር 13
3. ስጋቶችና የስጋት ማስወገጃ ስልቶች ........ 30
3.1. ስጋቶች ........ 30
3.2. የስጋት ማስወገጃ ስልቶች ........ 31
4. ማስፈፀሚያ ስልቶችና የክትትልና ግምገማ ስርዓት ........ 32
4.1. የማስፈጸሚያ ስልቶች ........ 32
4.2. የክትትልና ግምገማ ስርዓት ........ 34
4.2.1. የክትትልና ግምገማ መርሀ ግብር ........ 34
አባሪ ሁለት፡- የአቅም ልማት የካፒታል ፕሮጀክት ........ 46
የፕሮጀክቶች የፋይናንስ ፍላጎት ........ 46

## መግቢያ

አገራችንን በ2022 ዓ.ም የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ለማድረግ ሀገራዊ የአስር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህንን የልማት ጉዞ ለማሳካት የሚያስችሉ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችም ተነድፈው ለልማትና ዕድገት አመቺ የሆኑ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ እየተሰራ ሲሆን በቀጣይም የኢንዱስትሪ ፖሊሲና የተለያዩ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችን ጨምሮ አዳዲስ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛል፡፡

ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ለማሳካት ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ የሆነው የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ቁልፍ ሚና እንደሚኖረውና የኢኮኖሚ ሽግግር መምጣት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ለዚህም ለአምራቹ ዘርፍ ልማት ግብዓት የሚሆኑ ዕምቅ አቅሞች፣ ወጣትና በቀላሉ ሰልጥኖ ወደ ዘርፉ መቀላቀል የሚችል የሰው ሀብት፣ አመቺ የሆነ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች፣ ታዳሽ የኃይል አቅርቦት እየተስፋፋ መሆኑ፣ የመንገድና ሎጂስቲክስ አገልግሎት መሻሻል፣ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እየተስፋፋ መምጣቱ፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦት የተሟላላቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮችና ቀጠናዎች መስፋፋት፣ የዘርፉን አቅም የሚያሳድጉና የሚደግፉ ተቋማት መኖራቸው የዘርፉ ዋና ዋና ዕድሎችን አመላካች ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ እነዚህ ዕድሎች እንዳሉ ሁሉ ለዘርፉ ልማት ማነቆ ከሆኑ ተግዳሮቶች ውስጥ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ዕጥረት፣ የሀገራችን ባለሀብቶችና ማህበረሰብ ለአንዱስትሪ ልማት ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን፣ በቂና ጥራት ያላቸው ግብዓቶች በሀገር ውስጥ አለመገኘት፣ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነት፣ ዝቅተኛ የሥራ ባህል፣ ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ አቅም፣ ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በሚጠበቀው ደረጃ አለመከናወን እና ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተፈጠረ ያለመረጋጋትና የጸጥታ ችግሮች ተጠቃሽ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

ሰለዚህ በሀገራችን የአምራች ኢንዱስትሪው በኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ድርሻ ለማሳደግ እና የዘርፉን የመልማት አቅምንና መልካም አጋጣሚዎችን አሟጦ ለመጠቀም አገር አቀፍ የአምራች ኢንዱስትሪ አቅም ልማት ስትራቴጂ በዋናነት ኢንዱስትሪያላይዜሽን በተሟላ ተቋማዊ አቅም ለመምራት፣ መንግስታዊ የኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት የሰው ሀብት የአቅም ልማት ላይ ያተኮረ፣ ውጤታማ የመሰረተ ልማትና የሀብት አቅርቦትና አጠቃቀምን ከማሳደግ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ የአቅም ልማት የድጋፍ ማዕቀፍ ውጤታማ ከማድረግ እንዲሁም ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት መካከል በሚኖረው ጠንካራ አጋርነትና ግንኙነት የአቅም ልማቱን ውጤታማ

ለማድረግ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችንና አቅጣጫዎችን የያዘ የአምራች ኢንዱስትሪ አቅም ልማት ስትራቴጂ ተጠናቆ ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ የተከናወነ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንን የአምራች ኢንዱስትሪ የአቅም ልማት ስትራቴጂ እንደ ሀገር እስከ ታችኛው መዋቅር ተፈፃሚ ለማድረግ የማስተግበሪያ ዕቅድ ማዘጋጀት አስፋላጊ በመሆኑ ከሰባት ዓመታት የስትራቴጂው ትንተና (Strategic Matrix) መነሻ ያደረገ የቀጣይ ሶስት ዓመት ማስተግበሪያ ዕቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## 1. የአቅም ልማት ስትራቴጂ አጭር መግለጫ (Overview)

የአምራች ኢንዱስትሪው እንደሃገር የሚጠበቅበትን ሃገራዊ ሚና ለመጫወት የሚያስችለውን የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ አዘጋጅቶ ሃገራዊ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ቀርፆ እና አስፈላጊ የሆኑ ስትራተጂዎችን በማዘጋጀት ስራ ላይ በማዋል ለስኬቱ እየተጋ ይገኛል፡፡ የዘርፉ ልማት ለማፋጠን እና ውጤታማ የሆነ መዋቀራዊ ሽግግር ለማድረግ በርካታ ዕድሎች ቢኖሩም እነዚህን የልማት ዕድሎችን ለመጠቀም ማነቆ የሆኑትን ደግሞ ለመፍታት ከሆኑ ተግዳሮቶች ውስጥ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ዕጥረት፣ የሀገራችን ባለሀብቶችና ማህበረሰብ ለአንዱስትሪ ልማት ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን፣ ዝቅተኛ የሥራ ባህል፣ ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ አቅም እና ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በሚጠበቀው ደረጃ አለመከናወን ናቸው፡፡

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍና በሀገራዊ የአስር ዓመት የልማት ዕቅድና ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የአስር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ላይ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት፣ አንድ ሀገራዊ ራዕይን ለማሳካት በአብሮነት ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የቅንጅታዊ አሰራር አቅምን ለማጎልበት፣ ሙያዊ ስነምግባር የታነጸ በእውቀት፣ በክህሎትና አመለካከት የበቃ የሰው ሀብት አቅም ለመፍጠር፤ ችግር ፈቺ የስልጠና፣ የማማከር፣ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የቴክኖሎጂ ልማት ስርፀትና ሽግግር ለማከናወን የሚያስችል የመሰረተ ልማት፣ የቤተሙከራ እና ወርክሾፕ በሂደት ለማሟላት፣ ከፌደራል እስከ ክልልና የከተማ መስተዳድሮች በየደረጃው የአምራች ዘርፉን በሚደግፉ አካላት ላይ የሚስተዋለውን የመዋቅራዊ አደረጃጀት ተናባቢነት ለማስጠበቅ፣ በሀገራችን የዘርፉን አቅም ልማት ተግባራትን በፍጥነት ለማከናወን የሚያስችሉ ዕቅዶች፣ ኘሮግራሞች፣ ኘሮጀክቶችንና ኢንቲሼቲቮችን ቀርፆ ለመፈፀም ሚያስችል የአቅም ልማት ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖአል፡፡

እንደ ሃገር የተያዘውን በ2022 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ የማየት ራዕይን ለማሳካት ይህ የአቅም ልማት ስትራቴጂ ዕቅድ በዋናነት ተወዳዳሪ የሆነ አምራች ኢንዱስትሪ በመፍጠር የኢኮኖሚ መዋቅር ሽግግሩን እውን ለማድረግ በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ግቦችን ማሳካት የሚያስችል ሁለንተናዊ አቅም መገንባትና ማልማትን አጠቃላይ ዓላማ አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ በመነሳት አራት ዝርዝር ዓላማዎች የተቀረፁ ሲሆን እነዚህም ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፋ ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከት፣ በሙያዊ ስነምግባር እንዲሁም በጠንካራ የስራ ባህል የሚመራ የተሟላ መሰረተ

ልማት ያለው ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር፣ የአምራች ኢንዱስትሪውን ፍላጐትና ነባራዊ ሁኔታን መሠረት ባደረገ የሰው ሀብት አቅም ግንባታና ልማትን በማፋጠን ለበለጠ ውጤታማነት ማብቃት፤አምራች ኢንዱስትሪው የሰው ሃይሉን፣ የአመራሩን እና የቴክኖሎጂ አቅሙን እንዲያጎለብት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ምርትና ምርታማነቱን እና ተወዳዳሪነቱን እንዲያሳድግ ማስቻል፣ ቁልፍ አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ያላቸውን ሚና በውጤታማ ቅንጅታዊ አግባብ እንዲፈፅሙ የሚያስችል አቅም ለመፍጠር የሚያስችል ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡

የአቅም ልማት ስትረቴጂው ሲዘጋጅ በቅድሚያ የዳሰሳ ጥናት በጥልቀት በማካሂያድ ለስትራቴጂ ዕቅዱ መነሻ የሚሆኑ ሀሳቦችና ሰነዶችን በመተንተን በተለይ የአቅም ልማት ጽንሰ ሀሳብን፣ ሀገራዊ ዳሰሳን፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲና የአቅም ልማት ሃገራዊ አስቻይ ፖሊሲዎችንና የውጭ ሀገራት ተሞክሮ በመተንተን የነባራዊ ሁኔታዎች ላይ በተለይ የማኑፋቸሪንግ እድገት ሂደት በኢትዮጵያ፣ ያለፉት ዓመታት የአቅም ልማት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተግባርና ሀላፊነት ትንተና፣ የተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ትንተና የከባቢያዊ ሁኔታ ዳሰሳ፣ የደጋፊ ተቋማት አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ዳሰሳ ጥናት ግኝት፤ በተለያዩ አካላት የተዘጋጁ የስትራቴጂ ሰነዶች፣ ጥናቶች እና ፖሊሲዎች ዳሰሳ ተሰርቶ ግኝቶችን በግብዓትነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

የስትራቴጂ ሰነዱ የተሰሩ ዳሰሳዎችን በመጠቀም ውስጣዊ ተቋማዊ ሁኔታ ትንተና (SWOT)፣ የውጫዊ አካባቢ ትንተና (PESTL)፣ የባለድርሻና የተባባሪ አካላት ፍላጎት ትንተና፣ በተመረጡ አምራች ኢንዱስትሪዎች ላይ የተከናወነ የኬዝ ጥናት፣ ከስትራቴጂው ጋር የተዛመዱ አለማቀፋዊና ሀገራዊ ተሞክሮ እና በአቅም ልማት ዙሪያ ቀድመው የተጠኑ ጥናቶችን በመዳሰስ የአስር ዓመቱን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ፣ የአምራች ዘርፉን ፖሊሲና ስትራቴጂ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ አምስት ዋና ዋና ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች ተነድፈዋል፡፡

አምስቱ ስትራቴጂክ ጉዳዮች ኢንዱስትሪያላይዜሽን በተሟላ፣ ሁለንተናዊና የጋራ ተቋማዊ አቅም አለመመራቱ፣ የዘርፉ መንግስታዊ ተቋማት የሰው ሀብት የአቅም ግንባታና ልማት ደካማ መሆን፣ የመሰረተ ልማትና ቁሳዊ ሀብት ውስንነትና አጠቃቀም ችግር፣ ለኢንዱስትሪው የሚሰጠው የአቅም ግንባታና ልማት አገልግሎት የድጋፍ ማዕቀፎች ውጤታማ ያለመሆን፣ ከአቅም ግንባታና ልማት አኳያ ደካማ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲሁም የላላ ስትራቴጂካዊ ትብብርና አጋርነት መኖሩ የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህን የተለዩ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አቅም ልማት ስትራቴጂ ከ2016-2022 ለሰባት ዓመት ለመፈፀም በተለዩ 5 የስትራቴጂክ ጉዳዮች እና ስትራቴጂክ ጉዳዮቹ እንዲሳኩ የተቀመጡ 17 የስትራቴጂክ ግቦች ተቀርፀው ስትራቴጂክ ጉዳዮችን ለማሳካት የሚያስችል የቁልፍ ባለድርሻ አካላት ተፈፃሚ የሚያደርጓቸው … አቅጣጫዎች ተለይተዋል።
በተጨማሪም በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ለአቅም ግንባታ ልማት የተዘጋጁትን ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ለማሳካት ትኩረት ተሰጥቷቸው መፈፀም የሚገባቸውን ፕሮጄክቶች እና ስትራቴጂክ ኢንሼቲቮች ተለይተዋል። በዚሁም መሰረት በመካከለኛው ዘመን ከ2016-2018 ስትራቴጂውን ተፈፃሚ ለማድረግ የማስተግበሪያ ማዕቀፎችና ማስፈፀሚያ ስልቶች ተዘጋጅቷል።

# 2. የስትራቴጂው የትግበራ ማዕቀፍ (framework)

## 2.1. ርዕይ ተልዕኮና እሴቶች

**ርዕይ**

- በ2022 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ማየት፤

**ተልዕኮ**

- ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት፣ ጥናት ምርምር በማካሄድ፣ ቴክኖሎጂና የሰው ሃብት በማልማት፣ ግልፅና ውጤታማ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋት የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርትና ምርታማነት፣ ተወዳዳሪነትና ዕድገት ማረጋገጥ።

**እሴቶች**

- ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ስኬት መትጋት፣
- ሁልጊዜ ለመማርና ለለውጥ ዝግጁ መሆን፤
- ለፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግርና ተጠቃሚነት መስራት፣
- በቅንጅት መስራት፤
- ፈጠራና ልህቀት፤

## 2.2. የስትራተጂው ወሰን፣ መርሆዎችና ታሳቢዎች

### 2.2.1. የስትራቴጂ ዕቅዱ ወሰን

በሀገር አቀፍ ደረጃ በአምራች ዘርፍና ከዘርፉ ውጭ ባሉ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ዘንድ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ለማጐልበት የሚያስችሉ የሰው ኃይል ልማት፣ የአሠራርና አደረጃጀት፣ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና መሠረተ ልማት ዙሪያ አቅም ለመፍጠር የሚያስችሉ ተግባራትን በሁሉም የክልል፣ ከተማ አስተዳደር የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍና በፌዴራል በዘርፉና ከዘርፉ ውጭ ባሉ ተቋማት መዋቅር ላይ እንደየተቋማቱ እና ክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

### 2.2.2. መርሆዎች

የአምራች ኢንዱስትሪ አቅም ልማት ስትራቴጂውን ውጤታማ ለማድረግ በሚከተሉት መርሆዎች መሰረት እንደሚመራ አመላክቷል፡፡

- ውጤት ተኮርነት
- ዘርፈ ብዙነት
- ያልተማከለ አሰራር
- ችግር ፈቺነት
- ግልፅነትና ምላሽ ሰጪነት
- ተለማጭነት
- አካታችነትና አሳታፊነት
- ተጠያቂነት

### 2.2.3. የዕቅዱ ታሳቢዎች

የአምራች ኢንዱስትሪው የሰው ኃይል ልማትና ተወዳዳሪነት በበርካታ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ላይ በእጅጉ የሚመረኮዝ በመሆኑ ይህንን የአቅም ልማት ሥትራቴጂክ ዕቅድ በውጤታማነት ለመፈጸም ይቻል ዘንድ የሚከተሉት ጉዳዮች እንደሚሟሉ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

- የተሻሻሉ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂና የሕግ ማዕቀፎች ተግባር ላይ እንደሚውሉ እና የመንግስት ትኩረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል፤
- የዘርፉን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ከዘርፉ ጋር የተጣጣመ የሰው ኃይል ፍላጎት በወቅቱና በጥራት እንደሚሟላ፤

- በየደራጀው ያለ አመራር የአቅም  ልማትን እንደ ወሳኝ ተግባር ወስዶ በቁርጠኝነት እንደሚያስተገብር፤
- በመንግስት በኩል ለአቅም ልማት ትኩረት እንደሚሰጥና ለስልጠና ማዕከል፣ ለምርምር ልማት፣ ለላቦራቶሪ፣ ለወርክሾፕ፣ ለቢሮ ቁሳቁስ ማሟያ እና ለአጠቃላይ ለአቅም ልማትው አስፈላጊው በጀት እንደሚመደብ፤
- ተጀምረው የተቋረጡ እና አዳዲስ መጀመር የሚገባቸው  የአቅም ልማት ኘሮጀክት መርሃ ግብሮች እንደሚቀጥሉ፤
- የአምራች ኢንዱስትሪዎች የአቅም ልማትን እንደ ዋና ምርትና ምርታማነት ማሳደጊያ ስልት ተወስደው እንደሚተገብሩ፤
- ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች የስልጠናና የምርምር ልማት ክፍሎችን እንደሚያቋቁሙ እና መሰረተ ልማቶችን እንደሚያሟሉ፤
- ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ስትራተጂውን ወስደው ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥመው ለመተግበር ቁርጠኝነት እንደሚኖራቸው፤
- በትምህርትና ሥልጠና የተሻሻሉ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂና የሕግ ማዕቀፎች ማለትም የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፣ ምርምር ተቋማትና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ እና ወደፊት ይዘጋጃሉ የተባሉ የህግ ማዕቀፎች ተግባር ላይ እንደሚውሉ እና የመንግስት ትኩረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር እንደሚሻሻል፤
- የሀገራችን ፀጥታና ሠላም አስተማማኝ እንደሚሆን፤
- ከከፍተኛ ትምህርት እና ሌሎች የምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የዘርፉ የሰው ኃይል ልማት እና የምርምርና ቴክኖሎጂ ሥርፀትን ውጤታማ ለማድረግ የተቀናጀ አቅም በመፍጠር መሠረተ ልማቶችን በሙሉ አቅም መጠቀም እንደሚቻል፤
- የልማት አጋሮች ቀጣይነት ያለው ውጤታማ ድጋፍና ቅንጅት እንደሚኖራቸው፣

## 2.3. ዓላማዎችና በመካከለኛ ዘመን የሚጠበቅ ውጤት

### 2.3.1. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች አቅም ልማት የተቀመጡ ዓላማዎች

*ሀገራዊ የአምራች ኢንዱስትሪ አቅም ልማትን የተቀመጡ ስትራቴጂዎችን ከማሳካት አንጻር ቀጥሎ የተቀመጡት ዋና ዋና ዓላማዎች ትኩረት የተሰጣቸው ናቸው።*

1) ከዘርፋ ውጭ ላሉ የባለድርሻ አመራር አካላት በዘርፉ ላይ ያላቸውን ዕውቀትና አመለካከት በማሳደግ የኢንዱስትሪያላይዜሽንን እድገት በጋራ ማረጋገጥ የሚችል የአመራር አቅምና መዋቅራዊ አደረጃጀት መፍጠር፡፡
2) በዘርፉ የተቋማዊ ተምህሮ ስርዓትን በመዘርጋትና በመተግበር ጠንካራ የስራ ባህል ለመገንባት የሚስችል ሁለንተናዊ አቅም ቀጣይነት ባለው መልኩ በየደረጃው በሚገኘው አመራርና ባለሙያ ላይ መፍጠር፡፡
3) በዘርፉ ባሉ የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሙሉ ቁመና ለመደገፍ የሚያስችል የቢሮ ቁሳቁስ፡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ላብራቶሪና ወርክሾኘ መሠረተ ልማትን በማሟላት አቅም ልማት ስራውን ውጤታማ ማድረግ፡፡
4) የአቅም ልማትና ልማት አገልግሎት እና የድጋፍ ማዕቀፎች ውጤታማ ማድረግ፡፡
5) ቅንጅታዊና የትብብር አሰራር በማሻሻል አጠቃላይ ዘርፉ የሚፈልገውን ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት፤ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በጋራ በመስራት የዘርፉንም ሆነ የሌሎች ዘርፎች ችግር በጋራ የመፍታት አቅምን ማሳደግ፤ በዘርፉ የአቅም ልማትን ልማት ስራዎችን በአጋርነት ለመደገፍ ከሚፈልጉ ማናቸውም ተቋማትና ግለሰቦች ጋር ግንኙነትን በማጠናከር የተሟላ አቅም መፍጠር፡፡

### 2.3.2. በመካከለኛ ዘመን የሚጠበቅ ውጤት

የአቅም ልማት ስትራቴጂውን ወደ ትግበራ በማስገባት በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የሚጠበቁ ስኬቶችና ውጤቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1) ተቋማዊ የተሟላ ቁመና በመያዝ የአምራች ኢንዱስትሪንና ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ለመደገፍ የሚያስችል የኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት የሰው ሃይል ስምሪት አሁን ካለበት 49.35 በመቶ ወደ 70 በመቶ በማድረስ 15000 የአመራርና የባለሙያ የሰው ኃይል አቅም ግንባታን ማከናወን፤
2) የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የተጠሪ ተቋማት የህንፃ፣ የምርምር ወርክሾፖችና ፋሲሊቲዎች አሁን ካለበት 30 በመቶ ወደ 60 በመቶ ማድረስ፤
3) የቁልፍ ባለድርሻ አካላትንና የአምራች ኢንዱስትሪ አመራርና ባለሙያዎችን 107,062 የአቅም ልማት ስልጠና ማከናወን፤
4) በተጠናከረ የአመራር ሥርዓት የዘርፉን ችግር የመፍታት አቅም 85 በመቶ ማድረስ፤
5) በጥናት ላይ በመመስረት ሃገራዊ የኢንዱስትሪ ልማትና የሥራ ባህል ለማሳደግ የተቀየሱ አሠራሮችን 100% ተግባራዊ ማድረግ፤

## 2.4. የትኩረት መስኮችና ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች

### 2.4.1. ተቋማዊ አቅም ልማት

የተቋማዊ አቅም ልማት ሂደት በዋናነት ትኩረት ተሰጥቶ በቅድሚያ ሊሰሩ የሚገባቸው ቁልፍ ተግባራት መካከል፡-

- በትምህርትና ስልጠና የአመራርና የባለሙያዎች አቅም ልማት፤
- የስልጠና ማዕከል ግንባታ፤
- የምርምር ላቦራቶሪና ሰርቶ ማሳያ ግንባታ ፤
- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ማሟላት እና
- የዘርፉ አቅም ልማት ለማስፈፀም አደረጃጀትና የተለያዩ የአሠራር ስርዓት ማዘጋጀትና መተግበር

### 2.4.2. የፋይናንስና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የመጠቀም አቅም ማሳደግ

የአቅም ልማት ስራ ከፍተኛ የፋይናንስ አቅምና የተሟላ መሠረተ ልማት የሚጠይቅ በመሆኑ፡-

- ለአቅም ልማት ስልጠና፣ ለፋሲሊቲ ማደራጃና ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር ስራዎች የሚውል የአቅም ልማት ፈንድ ሥርዓት መዘርጋት፤
- ወደፊት የመዋዕለ ንዋይ እጥረትን ለመቅረፍ የወጪ ቁጠባ ስልቶች ተግባራዊ ማድረግ፤
- አምራች ኢንዱስትሪዎች ወይም የግል ኩባንያዎች ተሳትፎ እንዲጎለበት ማድረግ፤
- በዘርፉ ለሚደረገው የግል መዋዕለ ንዋይ የፋይናንስ ማበረታቻ ስርዓቶችን በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፤

- ለዘርፉ ልማት ከፍተኛ አስተዋጾ የሚኖራቸው፣ የላቀ ክህሎት እንዲሁም ኢንቨስትመንት የሚፈልጉ እና በመንግስት ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው የምርምር የትኩረት መስኮች በፕሮጀክት አመራር ስልት እንዲመሩ ማድረግ፤
- የልማት አጋሮችን ፈንድ ለአቅም ልማትና ለጥናትና ምርምር የሚውልበት ስልት ተቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ፤
- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀምን በሚፈለገው ደረጃ ማድረስ፤
- የተቀናጀ ስትራቴጂያዊ የሥራ አመራር ሥርዓትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር የሚያግዝ የመረጃ ሥርዓት እንዲተገበር ማድረግ፤
- የሚዘረጋው የኢኮቴ አሠራር ስርዓት የዘርፉን ዘላቂ መሰረት እንዲኖረው ከሚያስችሉ ስርዓቶች አንዱ የሆነውን የዕውቀት እቀባን በሚያረጋግጥ መልኩ አጋዥ እንዲሆን ማድረግ፤

### 2.4.3. የአምራች ኢንዱስትሪ የአቅም ልማት ስልጠና

በአለም አቀፍ ደረጃ አምራች ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪ ለማድረግ ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች አንዱ በአቅም ልማት ትምህርትና ስልጠና ብቃት እና ተሰጥዎ ያለው የሰው ኃይል ማፍራት አስገዳች የሆነበት ወቅት ነው፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ፡-

- የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ ትኩረት የሚደረግበት የስልጠና ርዕስ መለየት፣
- ወጥ የሆነ የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠና አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፣
- ከሌሎች የስልጠናና ትምህርት ተቋማት ጋር በመቀናጀት የንድፈሃሳብና የተግባር ስልጠና ለተጠቃሚው መስጠት፣
- በክልል ደረጃ የሚገኙ ሰልጣኞች አገልግሎቱን የሚያገኙበት ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፣
- ፕሮጀክት ተኮር የአሰልጣኞች ሰልጠና (Training of Trainers-TOT) ፕሮግራም መቅረጽ እና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በውጭ ከሚገኙ ተመሳሳይ ድርጅቶች በትብብር የአጭር ጊዜ የንድፈሃሳብና የተግባር ስልጠና ፕሮግራም በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በውጭ በትብብር የሚገኘውን አጫጭር ስልጠና በተቋማትና በኢንዱስትሪ ደረጃ ለልምድ ልውውጥ እንዲቀርብ ማድረግ፣

### 2.4.4. የጥናትና ምርምር አቅምን ማሳደግ

- የምርምርና ስርጸት መመሪያ መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ፣
- ለጥናትና ምርምር ኘሮጀክት በጀት መመደብና ለሀገር ውስጥ የትምህርት ተቋማት፣ የምርምር ማዕከላት የምርምር ኘሮጀክቶችን ኮንትራት በመስጠት ምርምሩን ማካሄድ፤
- በዓለም አቀፍ ባለሙያዎች የሚደረጉ ማናቸውም የዘርፉ የጥናትና ምርምር ስራዎች በአገሪቱ የምርምር አቅምን ለመገንባት መዋሉን ለማረጋገጥ የጥናትና ምርምር ኘሮጀክቶች አግባብነት ባለው የዘርፉ ተቋማት ውስጥ እንዲከናወን ማድረግና ኢትዮጵያዊያን የዘርፉ ባለሙያዎች ከዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ጋር እንዲሠሩ ማድረግ፣
- የተመራማሪዎች የማትጊያ ስርዓትን መቅረጽና (Incentive Packages) ተግባራዊ ማድረግ፣
- ተመራማሪዎች የምርምር ውጤታቸው ማቅረብ እንዲችሉ የምርምር ኮንፈረንሶችን፣ ሴሚናሮችንና ወርክሾፖችን በማዘጋጀት የምርምር ውጤቶች በስፋት የሚቀርቡበት መድረክ ማመቻቸት፣
- የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን የሚመራ የምርምርና የቴክኖሎጂ ካውንስል ማቋቋም፣

### 2.4.5. የአምራች ኢንዱስትሪውን እና የዘርፉ አስፈጻሚ አካላትን በዘላቂነት ማብቃት

- በዘርፉ በአመለካከት በእውቀትና በክህሎት ልምድና ብቃት ባዳበሩ ባለሙያዎች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፤
- ሞዴል አምራች ኢንዱስትሪዎች የድጋፍ መነሻ በማድረግ ድጋፉን መስጠት ፤
- ከንግድና አገልግሎት እና ከዩኒቨርስቲ ተመርቀው ወደ አምራች ዘርፍ ለሚቀለላቀሉ ግል ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት መደገፍ፤
- ያደጉ አገሮች ተሞክሮ እንደመነሻ ተጠቅሞ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር መጠቀም፤
- የተሰጠውን የስልጠና ድጋፍ በሙያ ደረጃ ምዘና አረጋግጦ ወደ ተግባር ማስገባት ብቁ ያልሆነው ክፍተቱን የሚሞላ ዳግም ስልጠና መስጠት፤
- በንግድ ልማት አገልግሎት (BDS) በማቀፍ የአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስተሪዎችን ችግር መለየትና መፍታት ሲሆን እነዚህን አገልግሎቶች በስፋት፣ በመዋቅር በተደገፈ አግባብ በመተግበር የአምራች ዘርፉን ውጤታማነት ማሳደግ፤

## 2.5. ስትራቴጂያዊ ግብ፣ የቁልፍ ውጤት አመላካቶችና ዝርዝር ተግባራት

በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ አቅም ልማት ስትራቴጂ ከ2016-2022 ለሰባት ዓመት ለመፈፀም የተለዩ 5 የስትራቴጂክ ጉዳዮች ተፈፃሚ ለማድረግ 17 የስትራቴጂክ ግቦች በመቅረፅ ግቡን ተግባራዊ ለማድረግ የሚስችሉ ተግባራት ተልይተዋል፡፡

በተጨማሪም በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ለአቅም ልማት የተዘጋጁትን ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ለማሳካት ትኩረት ተሰጥቷቸው መፈፀም የሚገባቸውን ስትራቴጂክ ኢንሼቲቮች ተለይተዋል፡፡ የአቅም ልማት ስትራቴጂውን ወደ ትግበራ ለማስገባትና ትኩረት ተሰጥቷቸው መተግበር የሚገባቸውን ኢንቬትቮች በአባሪ አንድ በዝርዝር እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

በዚሁም መሰረት በመካከለኛው ዘመን ከ2016-2018 ስትራቴጂውን ለመተግበር የተዘጋጀውን የድርጊት መርሃ ግብር የያዘ ሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2.5.1. የአምራች የአቅም ልማት ስትራቴጂ የመካከለኛ ዘመን የትግበራ የድርጊት መርሃ ግብር

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | **ስትራቴጂ1. *ኢንዱስትሪያላይዜሽን በተሟላ ተቋማዊ አቅም መምራት*** | | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ 1.1. *የባለድርሻ አመራር አካላት ኢንዱስትሪያላይዜሽን ላይ ያላቸውን እውቀትና አመለካከት ማሳደግ*** | | | | | | | | | | | | | |
| 1.1.1. | የእዉቀትና አመለካከት ክፍተቶችን መለየት | የቁልፍ ባለድርሻ አካላት አመራርን አቅም ልማት ዙሪያ ከአሠራር ስርዓት ዝርጋታ፣ የክፍተት ዳሰሳ ስራና የግንዛቤና የስልጠና ዓይነት የመለየት፣ የስልጠና ሞጁል የማዘጋጀትና ስልጠና የመስጠት እንዲሁም የተሞክሮ ልውውጥ ስራን ያካትታል፡፡ | በሰነድ ቁጥር | 1 | 1 | | | | 0.200 | 0.300 | | # | ### | ### |
| 1.1.2 | ክፍተቶችን የሚሞሉ ሰነዶችን ማዘጋጀት | | የተዘጋጁ የስልጠና ሰነዶች በቁጥር | 1 | 3 | 3 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር(ኢትዮጵያ ታምርት)፣ ኢኢል እና አኢልኢ | | 0.100 | 0.300 | 0.300 | ## | ### | ### |
| 1.1.3 | የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን ማከናወን | | በሰልጣኝ ቁጥር | 805 | 2000 | 1000 | | | 2 | 6 | 3 | # | ### | ### |
| 1.1.4. | የልምድ ልውውጥና የኢንዱስትሪ የመስክ ጉብኝቶች ማከናወን | | በቁጥር | 1 | 2 | 2 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ማኔጅመንት) | | 0.100 | 0.250 | 0.250 | ### | ## | ## |
| | **ግብ 1.2. የቢዝነስ ልማት አገልግሎትን (BDS) አቅም ልማትን ማጠናከር** | በኢትዮጵያ ታምርት ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር የአሠራር ስርዓት መዘርጋት፣ የአገልግሎት ፍላጐትና ተጠናቃሚን መለየት፣ ፖርትፎሊዮ (የአገልግሎት ማዕቀፍ በማዘጋጀት) | | | | | | | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| 1.2.1 | የአሰራር ስርዓት መዘርጋት | ተግባራዊ በማድረግ የአፈፃፀም ውጤታማነት መገምገምን ያጠቃልላል | በሰነድ | | 1 | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ማኔጅመንት)፣ ኢኢል | በመደበኛ በጀት | | 0.100 | | | | |
| 1.2.2. | ፍላጐትና ተጠቃሚዎችን መለየት | | በሰነድ | | 1 | 1 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (የመሰረተልማትና አቅም ልማት መ/ሥ/አሰ)፣ ኢኢል | በአጋር ልማት ድርጅት | | 1.5 | 1.5 | # | ### | ### |
| 1.2.3 | የአገልግሎት ፖርትፎሊዮ ማዘጋጀት | | በሰነድ | | 1 | | | | | | | ### | ### | ## |
| 1.2.4 | አፈፃፀሙን መገምገም | | በመቶኛ | | | 100 | ኢንዱስትሪ ሚ/ርና ኢኢል | | | | | ### | ### | ### |
| | **ግብ 1.3. ከአጋር አካላት ጋር የሚኖር ትብብርን ማጠናከር** | | | | | | | | | | | | | |
| 1.3.1 | የመንግስት፣ የማህበራትንና የአጋር አካላትን ትስስር ማጠናከር | የንግድና የዘርፍ ምክር ቤት፣ የሲቪክ፤ የአምራች ዘርፍ እና የሙያ ማህበራት የማደራጀትና የማጠናከር ስራን በማካተት የግል ተቋማት የአቅም ልማት ሚናቸውን እንዲወጡ የሚያደርግ ቁልፍ ተግባራት የሚያካትት ነው | በቁጥር | 1 | 2 | 2 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር(የብቃትና ፍቃድ አገልግሎት መ/ሥ/አሰ፣ ኢትዮጵያ ታምርት)፣ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ማህበራትና የልማት አጋር ድርጅቶች | አጋር የልማት ድርጅት | 1 | 2 | 2 | # | ## | ### |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | **ግብ 1.4. የአቅም ልማት የዕቅድ ዝግጅት፣ክትትልና ግምገማን ማጠናከር** | ከሚ/ር መ/ቤት እስከ ተጠሪ ተቋማት የተናበበና የጋራ ዕቅድ ከማዘጋጀት እስከ ክልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት የተናበበ ዕቅድ ማዘጋጀትና ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በስርዓት ላይ የተመሠረተ ድጋፍ የማድረግ ስራን ያጠቃልላል | | | | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ስትራተጂክ ጉዳዮች መ/ሥ/አስ፣ የብቃትና የሰው ሃብት አስ/ሥ/አስ፣ የመሰረተ ልማና አቅ/ግ/መ/ሥ/አስ፣ አኢልኢ፣ ኢኢል፣ ክልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት | በመደበኛ | | | | | | |
| 1.4.1 | የጋራ ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግባር | | በቁጥር | 1 | 2 | 2 | | | **1.5** | **2** | **2** | **#** | **###** | **###** |
| 1.4.2 | ክትትልና ግምገማ ስራ መፈፀም | | በቁጥር | 1 | 4 | 4 | | | **0.300** | **1.2** | **1.2** | **##** | **###** | **###** |
| | **ስትራቴጂ 2. መንግስታዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት የሰው ሀብት የአቅም ልማት** | አምራች ኢንዱስትሪውን የሚደግፉ በመንግስት መዋቅር ያሉ ደጋፊ ተቋማት ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰማራውን የስው ኃይል ፍላጐት ከመተንተን በዕውቀት፣ በክህሎትና በልምድ የበቃ የሰው ሃብት ፍላጐትን በጥናት በመለየትና ለገበያው ዕውቀት፣ በስነ ምግባርና በክህሎት የበቃ የሰው ኃይል የሚቀርብበትና ወደ ዘርፍ የሚቀላቀሉ የሰው ኃይል ከመነሻው በዘርፋ ግንዛቤን ይዘው ወደ ኢንዱስትሪው እንዲቀላቀሉ ግንዛቤ የመፍጠር ስራን ያካትታል | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ 2.1. የዘርፋን የሰው ሀብት ማሟላት** | | | | | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (የብቃትና ሰው ሀብት አስ/ሥ/ አሰፈፃሚ) ፣ አኢልኢ፣ኢኢል፣ ክልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት | | | | | | | |
| 2.1.1 | የሰው ሃብት ትንተና (Human Resource Analysis) | | በሰነድ | | 1 | | | መደበኛ በጀት | **0.100** | **0.500** | | **#** | **##** | **##** |
| 2.1.2 | የሰው ሃብት ቅጥር/ዝውውር/ደረጃ እድገት ማከናወን | | በመቶኛ | | 60 | 70 | | | | **0.050** | **0.050** | **#** | **###** | **###** |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| 2.1.3 | በግል ባለሃብቱ እና በመንግስት የሚተገበር የኢንዱስትሪ ኤጀንት የሚኖርበት ሥርዓት መዘርጋት | | በሰነድ | 1 | | | | በመደበኛ በጀት | 0.50 | | | # | ### | ### |
| 2.1.4 | ባለሙያዎችን መቅጠርና ወደ ስራ ማስገባት | | በባለሙያዎች ቁጥር | | 70 | 100 | | በኢንዱስትሪውና በአጋር ልማት | | 12 | 35 | # | ### | ### |
| 2.1.5 | ወደ ተቋማቱ ለሚቀላቀሉ የሰው ኃይል በዘርፉ ዙሪያ ተገቢውን የቅድመ ስራ ግንዛቤ የማስጨበጥ | | በመቶኛ | | 100 | 100 | | በመደበኛ በጀት | | 0.200 | 0.200 | ### | ### | ### |
| | **ግብ 2.2. የመንግስት የኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት የሰው ሀብት ልማት ውጤታማነት** | | | | | | | | | | | | | |
| 2.2.1 | የፍላጐት ዳሰሳ ማከናወን | የኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት ሙሉ ቁመና ይዘው ዘርፉን በተሟላ አግባብ ለመደገፍ የሚያስች ል የሰው ሃብት አቅም ክፍተትንና ፍላጐትን በመዳሰስ ተከታታይነት ያለው የአቅም ልማት ከአጭር ጊዜ የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠና ከመስጠት እስከ ረጅም ጊዜ ስልጠና/ የሁለተኛና የሶስተኛ ዲግሪ/ ትምህርትን በመስጠት የሰው ሃብት ብቃትን ማሳደግ ያካተተ ነው | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (የብቃትና ሰው ሀብት አስ/ሥ/ አሰፈፃሚ እና የመሰረተ ልማትና አቅም ልማት መ/ሥ አ)፣ አኢል (ትም/ሥልጠና ዴስክ)፣ ኢኢል፣ ክልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ | መደበኛ በጀት | 0.100 | 0.100 | 0.100 | ## | ### | ### |
| 2.2.2 | የኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት የሰው ኃይል የመረጃ ቋት ማደራጀት | | በመቶኛ | 25 | 100 | | | | 0.010 | 0.090 | | # | ### | ### |
| 2.2.3 | የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት (ለሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት እና ለክልል/ከተማ መስተዳደር) | | በቁጥር | | 11000 | 13000 | | | | 90 | 105 | ## | ### | ### |
| 2.2.4 | የረጅም ጊዜ ስልጠና መስጠት | | | 25 | 55 | 65 | | | | 7.8 | 10 | # | ## | ## |
| 2.2.5 | የአመራር ስልጠና መስጠት | | | | 2000 | 2000 | | | | 16.5 | 16.5 | ## | ### | ### |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| 2.2.5 | የስልጠናውን ፋይዳ መገምገም | | | | 1 | 1 | ደጋፊ ተቋማት | | | **0.500** | **0.500** | ## | ### | ### |
| | **ግብ 2.3. ተቋማዊ መማማር/ Develop learning organization እና የስራ ባህልን ማጎልበት/ Develop organization Culture** | | | | | | | | | **3** | **3** | | | |
| 2.3.1 | ተቋማዊ ተምህሮትን የሚያግዝ ሥርዓት መዘርጋት እና መተግበር | ተቋማዊ ተምህሮ ሲባል ራስን ከማወቅ አንስቶ እስከ ሥርዓታዊ አስተሳሰብ (System Thinking) የሚደርስ በየደረጃው የጋራ ራዕይን ለማምጣት አስተሳሰብን ከመቅረፅ ጋር ተያያዥነት አለው። ለዚህ የሚያግዝ ሥርዓትን መዘርጋት የዚህ ግብ ዋና መሳሪያ ነው፡፧ ተቋማዊ ተምህሮን ተደራሽነት፣ ፍትሃዊ በሆነ አግባብ ለመምራት ምቹ የስራ ከባቢ በመፍጠር የኢንዱስትሪን ስነ ምግባር የሚያስጠብቅ ሰነድ በማዘጋጀት የማስረፅ ስራ ከመስራትና ብቁ ሲቪል ሰርቪስ ከመፍጠር የማበረታቻ ሥርዓት የመቅረፅና ተቋማዊ ባህልን በመገንባት የኢንዱስትሪ ባህል ግንባታን ስራ ያካተተ ነው | በመቶኛ | | 100 | 100 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር ማናጅመንት፣ አኢልኢ፣ ኢኢል፣ ከልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት | መደበኛ ና የአጋር ልማት ድጋፍ | | **0.100** | **0.090** | # | ### | ### |
| 2.3.2 | የዘርፉን ሙያተኞች የሙያ ሥነ-ምግባርን የሚያስጠብቅ ስርዓት መቅረፅና መተግበር | | ሰነድ በቁጥር | | 1 | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር ማናጅመንት | | | **0.500** | **0.500** | # | ### | ### |
| 2.3.4 | የማበረታቻ ስርዓት መቅረፅና መተግበር | | በቁጥር | | 1 | 1 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (የሴቶች ወጣቶችና የማህ/አካቶ ትግበራ መ/ሥ/ አሰ፣ አኢልኢ፣ ኢኢል፣ ከልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት | | | **0.500** | **0.500** | # | ### | ### |
| 2.3.5 | ተቋማዊ ባህልንና ማህበራዊ ክህሎትን ተሳትፎ ማሳደግ | | በመቶኛ | | 40 | 60 | | ተጨማሪ ገቢን በመፍጠር | | **0.400** | **0.410** | # | ### | ### |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት /የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| 2.3.6 | የኢንዱስትሪያላዜሽን ውቅረ ልቡና ማስረፅ | | በቁጥር | | 2 | 2 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር መሰረተልማትና አቅም ልማት መ/ሥ/አስ ፣ አኢልኢ፣ ኢኢል፣ ክልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት | በመደበኛ በጀት | | 1.5 | 1.5 | | | |
| | **ግብ 2.4. ተቋማዊ እውቀቶች በማዕከላዊነት በማስተዳደር በባለሙያዎች መካከል የእውቀት ሽግግር እንዲኖርና እንዲዳብር ማድረግ** | | | | | | | | | | | | | |
| 2.4.1 | የእውቀት ማቀብ / Archive Knowledge/ አሠራር ስርዓት መዘርጋት | በተቋም ደረጃ ያሉ እውቀቶችን በመለየትና በተለያየ መንገድ በማቀብ በተለይ ከውጭ ጉብኝት፣ ከስልጠና፣ ከተቋም የተለያዩ ሰነዶችን በማደራጀት የመያዝና ለሌሎች የማስተላለፍ እና ተተኪን የማፍራት ስራ ያካትታል | ሰነድ | 1 | | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር(ብቃትና ሰው ሃብት አስተዳደር ሥ/አስ እና ስትራቴጂክ ጉዳ/ሥ/አስ) ፣ አኢልኢ፣ ኢኢል፣ ክልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት | መደበኛ በጀትና አጋር የልማት ድርጅት ድጋፍ | | | | ## | ### | ### |
| 2.4.2 | የእውቀት ዓይነቶች የመለየትና የማቀብ ስራ ማከናወን | | በቁጥር | 1 | 4 | 10 | | | | 0.100 | 0.500 | ## | ### | ### |
| 2.4.3 | እውቀት ማሰራጨትና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ | | በመቶኛ | | 50 | 70 | | | | 1 | 1.5 | # | ## | ## |
| 2.4.4 | የተሻሉ ተሞክሮዎችን የመቀመር፣ የማስፋትና የመተግበር ስራ ማከናወን | | በቁጥር | | 2 | 3 | | | | 0.400 | 1 | # | ## | ## |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | **ግብ 2.5. ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች የሰው ሀብት የአቅም ልማት ድጋፍ** | | | | | | | | | | | | | |
| 2.5.1 | ክፍተት ዳሰሳ ስራ ማከናወን | ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ ክልሎችና ተቋማት የሚለይ መስፈርት በማዘጋጀትና በክልሉ ያዳለውን ተጨባጭ ሁኔታ ያለውን ክፍተት በመዳሰስ የድጋፍ ማዕቀፍ በማዘጋጀት በኘሮጀክት፣ በኢንቬቲቭ በመቅረፅ ወደ ተግባር በመቀየር የቅርብ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ስራን ያካትታል | ሰነድ በቁጥር | | 1 | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (የመሰረተልማትአቅ/ግንባታ መ/ሥ/አስ፣ ኢ.ኢ.ል፣ | መደበኛ በጀትና አጋር የልማት ድርጅት ድጋፍ | | **0.500** | | **##** | **##** | **##** |
| 2.5.2 | የልዩ ድጋፍ ማዕቀፍ ማዘጋጀት | | ሰነድ በቁጥር | | 1 | 1 | | | | **0.500** | **0.500** | **##** | **##** | **##** |
| 2.5.3 | የአቅም ልማትና የማማከር አገልግሎት ድጋፍ መስጠት | | በመቶኛ | 45 | 60 | 75 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (የመሰረተልማትአቅ/ግንባታ መ/ሥ/አስ፣ አኢልኢ፣ ኢ.ኢ.ል፣ ክልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት | መደበኛ /አጋር የልማት ድርጅት ድጋፍ | **0.800** | **3.2** | **5.5** | **#** | **###** | **###** |
| 2.5.4 | የክትትልና ድጋፍ ስራ ማከናወን | | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (የመሰረተልማትአቅ/ግንባታ መ/ሥ/አስ፣ ስትራቴጅክ ጉዳይ ሥ/አሰ እና የለውጥ 1ጉዳዮች ሥ/አሰ) ኢ.ኢ.ል፣ | መደበኛ | **0.200** | **0.800** | **1** | **##** | **###** | **###** |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | **ስትራቴጂ 3. ውጤታማ የመሠረተ ልማትና የሀብት አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሳደግ** | | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ 3.1 ተጨማሪ የፋይናንስ ምንጭን ማበራከት እና የአቅም ልማት በጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሻሻል** | | | | | | | | | | | | | |
| 3.1.1 | የውስጥ ገቢ የህግ ማዕቀፍ ስርዓት ማዘጋጀት | | ሰነድ | 1 | | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር(ሚኒስቴር ፅ/ቤት እና የህግ አገልግሎት ሥ/አስ) | መደበኛ በጀት | **0.100** | | | ## | ### | ### |
| 3.1.2 | የፋይናንስ አቅምን የማሳደግና ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ | የፋይናንስ አቅምን ለማጠናከር የሚያስችል ከሚሰጡ አገልግሎቶች የሚገኙ ገቢን ለመጠቀም የሚያስችል የአሠራር ስርዓት በመዘርጋትና በማስፈቀድ ከተለያዩ አጋር አካላት ኘሮጀክቶችን በመቅረፅ ተጨማሪ የፋይናንስ ፈንድ የማግኘት፣ የቴክኒክ ድጋፍ በማፈላለግ የሚገኙ ድጋፎችን በአግባቡ ስራ ላይ ማዋልን በአጠቃላይ የአቅም ልማት ከፍተኛ የፋይናንስ አቅም የሚፈልግ በመሆኑ የምርምር ፈንድን የማቋቋምና ስርዓት ዘርግቶ ወደ ተግባር እንዲገባ የማድረግ ስራ ያጠቃልላል | በመቶኛ | 50 | 65 | 75 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ማኔጅመንት)፣ አኢልኢ፣ ኢኢል፣ ክልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት | የውስጥ ገቢና የአጋር ልማት ድጋፍ | **0.100** | **0.500** | **0.500** | # | ### | ### |
| 3.1.3 | የፋይናንስ አጠቃቀምን በኢ.ኮ.ቴ በተደገፈ አሰራር ተግባራዊ ማድረግ | | በመቶኛ | 70 | 75 | 80 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ኢ.ኮ.ቴ.ሥ/አ እና የግዥና ፋይናንስ ሥ/አስ)፣ አኢልኢ፣ ኢኢል፣ ክልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ | የውስጥ ገቢና የአጋር ልማት ድጋፍ | | | | ### | ### | ### |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | | | | | | | ደጋፊ ተቋማት | | | | | | | |
| 3.1.4 | የምርምር ፈንድ የሚቋቋምበት ስርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ | | በቁጥር | | 1 | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ማኔጅመንት) አኢልኢ፣ ኢኢል፣ | መደበኛ በጀት | | **0.500** | | **#** | **###** | **###** |
| | **ግብ 3.2 ለሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ፣ ጤናማና ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ አካባቢ መፍጠር** | | | | | | | | | | | | | |
| 3.2.1 | የፋስሊቲ ዳሰሳ ስራ ማከናወን | የስራ ቦታን ለሠራተኛውና ለአገልግሎት ተቀባዩ ምቹ ከማድረግ አንፃር ከተቋማት የስራ ባህሪ ጋር የተጣጣመ ስታንዳርድ የማዘጋጀት፣ የሚያስፈልጉ የፋሲሊቲ ፍላጎት ዳሰሳ ስራ በመፈፀም ፋሲሊቲውን የማሟላት ስራ በማከናወን ምቹ የስራ ከባቢውን ዘላቂ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ሊን ወይም የካይዘን ፍልስፍና ተግባራዊ የማድረግ ተግባራትን ያጠቃልላል | ሰነድ | | 1 | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (የብቃትና የሰ/ሃ/አሰ/ሥ/አስ እና የተቋማዊ ለውጥ ሥ/አስ)፣ አኢልኢ (ካይዘን ልህ/ማ)፣ ኢኢል | መደበኛ በጀትና አጋር የልማት ድጋጅት ድጋፍ | | **0.500** | | **##** | **##** | **##** |
| 3.2.2 | ስታንዳርድ ማዘጋጀት | | ሰነድ | | 1 | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (የብቃትና የሰ/ሃ/አሰ/ሥ/አስ እና የተቋማዊ ለውጥ ሥ/አስ)፣ አኢልኢ (ካይዘን ልህ/ማ)፣ ኢኢል | | | **0.500** | | **##** | **###** | **###** |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| 3.2.3 | የቢሮ ህንፃ ግንባታ ስራ ማከናወን(ለኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ ለኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት፣ ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት/ የማኑፋክቸሪንግ ቴ/ኢ/ም/ል/ማ፣ የኬ/ኮ/ም/ል/ማ እና የም/መ/ም/ል/ማ) | | የስራዉ ደረጃ በመቶኛ | 20 | 50 | 70 | | **መደበኛ ካፒታል በጀት** | **500** | **4500** | **3000** | **#** | **###** | **###** |
| 3.2.4 | ፋሲሊቲ የማሟላት ስራ ማከናወን | | በመቶኛ | | 50 | 50 | **ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ማኔጅምንት)፣ አኢልኢ ማኔጅምንት)፣ ኢኢል (ማኔጅምንት)** | **መደበኛ ካፒታል በጀትና አጋር ልማት** | | **1000** | **500** | **#** | **###** | **###** |
| 3.2.4 | ሊን/ካይዘን… ማኔጅመንት ተግባራትን ማከናወን | | በመቶኛ | 50 | 100 | 100 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (የብቃትና የሰ/ሃ/አሰ/ሥ/አስ እና የተቋማዊ ለውጥ ሥ/አስ)፣ አኢልኢ (ካይዘን ልህ/ማ)፣ ኢኢል (በአጠቃላይ በከይዘን ልህቀት ማዕከል መሪነት) | **መደበኛ በጀት** | **0.100** | **0.200** | **0.250** | **#** | **##** | **##** |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | **ግብ 3.3 የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዝርጋታንና የመጠቀም አቅምን ማሳደግ** | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ከማሟላት ጀምሮ በተለይ አገልግሎቱን ለማዘመን የሚያስችሉ አገልግሎቶችን በኦንላየን ከመስጠትና ለሚሰጡ አገልግሎቶችና ለተቋም ስራ አቅም የሚሆኑ የተለያዩ የኤንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የተለያዩ ሶፍት ዌሮችን የማልማትና ወደ ትግበራ የመቀየር ተግባራትን ያካትታል | | | | | | | | | | | | |
| 3.3.1 | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረት ልማት መዘርጋት | | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ኢ.ኮ.ቴ.ሥ/አ እና የአንድ ማዕከል አገልግሎት)፣ አኢልኢ፣ ኢኢል፣ ክልልና ከተማ መስተዳድር ኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት | መደበኛ በጀትና አጋር የልማት ድጋጅት ድጋፍ | | 40 | 48 | ## | ### | ### |
| 3.3.2 | አገልግሎቶችን ማዘመን | | በቁጥር | 28 | 30 | 40 | | | | | | # | ### | ### |
| | **ስትራቴጂ 4. የአምራች ኢንዱስትሪ የአቅም ልማት የድጋፍ ማዕቀፍ ውጤታማ ማድረግ** | | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ 4.1 የአምራች ኢንዱስትሪውን የሰው ሀብት አቅም ሊያጎለብት የሚችል የስልጠና ተደራሽነትን ማስፋት** | በአምራች ዘርፉ ያሉ የክህሎት ክፍተትና የፍላጐት ደሰሳ ጥናት ስራ በማከናን ለኢንዱስትሪው የሚመጥኑ የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ሞጁሎችን በማዘጋጀት የስልጠና ከባቢ ሁኔታ ምቹ በማድረግ የአጫጭር ጊዜ ስልጠና የመሰጠት እንዲሁም ተደራሽነትን ለማስፋት በኢንዱስትሪ ውስጥ ስልጠና የሚሰጡ ፋብሪካዎችን የመለየትና ስልጠና የመስጠት ስልጠናው የኢንዱስትሪው አመራርን ለማብቃት የሚያስችሉ ሞጁሎችና የስልጠና ማቴሪያል በማዘጋጀት በአጠቃላይ | | | | | | | | | | | | |
| 4.1.1 | የክፍተትና ፍላጐት ዳሰሳ ማከናወን | | ሰነድ | 1 | 1 | 1 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ወጪና ተኪ ምርቶች ሥ/አስ)፣ አኢልኢ (ትምህርትና ሥ/ዴስክ)፣ ኢኢል | መደበኛ በጀት | 0.500 | 1 | 1 | # | ### | ### |
| 4.1.2 | የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት | | በቁጥር | 27,400 | 30,000 | 35,000 | | | 20 | 20 | 24 | # | ### | ### |
| 4.1.4 | የአመራር ስልጠና መስጠት | | በቁጥር | 300 | 900 | 1200 | | | 2 | 3 | 5 | # | ### | ### |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | | የተሰጡ ስልጠናዎች ፋይዳ የመገምገም ስራን ያጠቃልላል | | | | | (የአቅም ልማት መ/ሥ/አስ)፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች | | | | | | | |
| 4.1.5 | የኢንዱስትሪ ውስጥ ስልጠናን (Training Within Industry) ለመስጠት የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ስራ ማከናወን | | በቁጥር | 1 | | | በኢትዮጵያ ታምርት | መደበኛ በጀት | **0.300** | | | | | |
| 4.1.6 | የኢንዱስትሪ ውስጥ ስልጠናን (Training Within Industry) መተግበር | | የጀመሩ ኢንዱስትሪዎች በቁጥር | | 10 | 20 | አኢልኢ (ከይዘን ልህ/ማ፣ ኢትዮጵያ ታምርት)፣ ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች | በወጪ መጋራት የሚሸፈን | | **10** | **20** | **#** | **###** | **###** |
| 4.1.7 | የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን ማፍራት | | በቁጥር | | 300 | 400 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ አኢልኢ፣ ኢኢል (ማኔጅመንቱ) | በመደበኛና አጋር ልማት | | **5** | **7** | **#** | **###** | **###** |
| 4.1.8 | የሰው ሃብት ትንተና (Human Resource Analysis) | | በሰነድ | | 1 | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ወጪና ተኪ ምርቶች መ/ሥ/አስ)፣ አኢልኢ (ትምህርትና ሥ/ዴስክ እና ማዕከላት)፣ ኢኢል | በአጋር ልማት | | **25** | **65** | **#** | **##** | **##** |
| 4.1.9 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በመንግስት ያሉ ደጋፊ አካላት የሰው | | በሰነድ | | | 1 | | | | | **60** | **#** | **###** | **###** |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | ሃብት ፍላጐት ጥናት (Human Resource Demand Analysis) | | | | | | (የአቅም ልማት መ/ሥ/አስ)፣ | | | | | | | |
| 4.1.10 | የስልጠናውን ፋይዳ መገምገም | | ሰነድ | | 1 | 1 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ወጪና ተኪ ምርቶች መ/ሥ/አስ)፣ አኢልኢ (ትምህርትና ሥ/ዴስክ እና ማዕከላት)፣ ኢኢል (የአቅም ልማት መ/ሥ/አስ)፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች | መደበኛ በጀት | | 3 | 3 | ## | ## | ## |
| | **ግብ 4.2 ለአምራች ኢንዱስትሪው በአቅም ልማት ዙሪያ በተሰጡ አገልግሎቶች የተገኙ ውጤቶችን ማዝለቅ** | የአቅም ልማት ስራዎችን ዘላቂ ለማድረግ በተለይ አቅም ልማቱን ተግባራዊ የሚያደርጉ ተቋማትን ከመደገፍ አንፃር የማበረታቻ ስርዓት በማዘጋጀት ወደ ትግበራ በማስገባት፣ በተለይ በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ በቁርኝት ኘሮጀክት የአቅም ልማት ስራዎችን በማጠናከር በኢንስቲትዩት ቁመና ላይ በመድረስ ከሌሎች ሃገራት ክፍተት ያለበት ዘርፎችን በመለየትና የቤንችማርኪንግ አገልግሎት የተሻለ ተሞክሮ እንዲተላለፍ የማድረግና እንዲሁም ትውልድን ለመቅረፅ የሚያስችል በትምህርት ተቋማት የኢንዱስትሪ የተጓዳኝ ካሪኩለም እንዲዘጋጅ የማድረግ እና ሁነቶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ የማድረግ ተግባራትን ያካትታል። | | | | | | | | | | | | |
| 4.2.1 | የቤንችማርኪንግ አገልግሎት መስጠት(በጨርቃጨርቅ የተጀመረውን መጨረስና የቆዳና ቆዳ ውጤቶች እና በአነስተኛና መካከለኛ ማስጀመር) | | በቁጥር | | 2 | 2 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ወጪና ተኪ ምርቶች መ/ሥ/አስ)፣ አኢልኢ (ማዕከላት)፣ ኢኢል፣ | በመደበኛ ካፒታል በጀት | 6 | 24 | 35 | # | ### | ### |
| 4.2.2 | የማበረታቻ ፓኬጆችን መቅረፅና መተግበር | | በመቶኛ | | 50 | 75 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ማስፋፊያና ማበረታቻ መ/ሥ/አስ)፣ | | | 0.500 | 0.800 | # | ### | ### |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | | | | | | | አኢልኢ (ማዕከላት)፣ ኢኢል፣ | | | | | | | |
| 4.2.3 | ትውልድን ከመቅረፅና በዘርፉ ቁልፍ ሚና ያላቸውን አካላት የማበረታቻና የሁነት ዝግጅቶችን መፈፀም | | በቁጥር | | 1 | 1 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር (ኢትዮጵያ ታምርት)፣ | መደበኛ በጀትና አጋር የልማ ት ድርጅት ድጋፍ | | **2** | **2** | ## | ### | ### |
| | **ስትራቴጂ 5. የአቅም ልማት ከሚሰሩ ተቋማት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር እና ስትራቴጂካዊ ትብብር መፍጠር** | | | | | | | | | | | | | |
| | **ግብ 5.1 ከከፍተኛ ትምህርት እና ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር ያለን የትብብርና ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር** | | | | | | | | | | | | | |
| 5.1.1 | በትስስሩ ያሉ ተቋማት አሰራር ስርዓት መዘርጋት | በትስስሩ መካተት የሚገባቸውን ተቋማት በመለየትና የትስስር አሠራር ስርዓት በመዘርጋት፣ የተግባር ስልጠና ለሚሰጡ ተቋማት የማበረታቻ ስርዓት በማዘጋጀትና በመተግበር፣ ለኢንዱስትሪው አጋዥ የሆኑየከፍተኛ ትምህርት ስርዓተ ትምህርቶችን ከትምህርት ሚ/ር፣ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በጋራ የመስራትን ለኢንዱስትሪው የሚፈልገውን መካከለኛ የሙያ ደረጃ ያላቸውን የሙያ ደረጃዎች በመለየት ለኢንዱስትሪው አጋዥ የሆኑ ስርዓተ ትምህርቶችን ከስራና ክህሎት ሚ/ር እና ከቴ/ት/ስ/ተቋማት እና | ሰነድ | 1 | | | ትምህርት ሚኒስቴር፣ ሥና ክህሎት ሚኒስቴር፣ አምራች ዘርፍ ማህበራት እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር( የመሰረተ ልማትና አቅም ልማት መ/ሥ/አስ፣ ማስፋፊያና ማበረታቻ | መደበኛ በጀትና | **0.080** | | | ## | ### | ### |
| 5.1.2 | የተግባር ስልጠና የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት | | ሰነድ | | 1 | | | | | **0.080** | | # | ### | ### |
| 5.1.3 | ለአምራች ኢንዱስትሪው አስፈላጊ የሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ስርዓተ- | | ሰነድ | | 3 | 4 | | አጋር የልማት ድጋጅት ድጋፍ | | **3** | **4** | # | ### | ### |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | ትምህርቶች እንዲቀረጽ እና እንዲከለስ ማድረግ | ከኢንዱስትሪው የተውጣጡ ባለሙያን በመያዝ በጋራ የመስራትን፤ እንደ ሃገር የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ያሉ መሠረተ ልማትና ፋሲሊቲዎችን ቆጠራ የማድረግና በጋራ መጠቀም የሚያስችሉ አሠራሮችን ተግባራዊ ማድረግ፣ በዩኒቨርስቲ ኢንዱስትሪ ትስስር የኤክስተርንሽፕ፣ ኢንተርንሽፕ፣ የትብብር ስልጠና፣የምርምርና የማማከር አገልግሎትን የማከናወን እንዲሁም የተሻለ ክህሎት ያላቸውን ተመራቂ ተማሪዎችን በመለየት ከፋብሪካ ጋር ስራ እንዲያገኙ የማስተሳሰር ስራዎችን ያጠቃልላል | | | | | መ/ሥ/አስ እና ኢትዮጵያ ታምርት) | | | | | | | |
| 5.1.4 | የቴ/ሙ/ የሙያ ደረጃዎች እንዲቀረጽ እና እንዲከለስ ማድረግ | | ሰነድ | 4 | 8 | 12 | | | 1.5 | 3 | 4.5 | # | ### | ### |
| 5.1.5 | በትስስሩ ያሉ አካላት ያላቸውን ለዘርፉ ጠቃሚ የሆኑ መሰረተ-ልማቶችን መለየት እና ለጋራ ሥራ በጋራ መጠቀም | | በመቶኛ | | 40 | 60 | ዩኒቨርስቲ፣ ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የምርምር ተቋማት እና አምራች ኢንዱስትሪ | መደበኛ በጀትና | | 0.500 | 0.500 | # | ### | ### |
| 5.1.6 | የዩኒቨርስቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር ማዕቀፎችን ተግባራዊ ማድረግ | | በቁጥር | 6 | 6 | 6 | ትም/ት ሚኒስቴር፣ ሥራና ክህሎት ሚ/ር፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር( የመሰረተ ልማትና አቅም ልማት መ/ሥ/አስ፣ ኢትዮጵያ ታምርት)፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች፣ የምርምር ተቋማት፣ አምራች ኢንዱስትሪ እና ኢኢል | መደበኛ በጀትና | | 20 | 24 | ## | ### | ### |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ 2016 | 2017 | 2018 | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር 2016 | 2017 | 2018 | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.1.7 | የቴ/ሙ/ት/ስ/ተቋማት የቴክኖሎጂ የኢንኩቤሽን ማዕከላት እንዲሆኑ ቴክኒካል ድጋፍ ማድረግ | | በመቶኛ | | 4 | 7 | ቴ/ሙ/ት/ ስ/ተ፣ አኢልኢ | አጋር የልማት ድርጅት | | 1 | 2 | # | ### | ### |
| | **ግብ 5.2 የጋራ ጥናትና ምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግርና ሥርፀትን ማሳደግ** | የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚጠበቅበትን ሃገራዊ የእድገት አስተዋጽዖ ማበርከት እንዲችል በምርምር፣ በቴክኖሎጂ ልማት እና ሽግግር ለመደገፍ የህግ ማዕቀፍ የያዘ ፖሊሲ በማዘጋጀት በሃገር ደረጃ የማኑፋክቸሪንገ ዘርፍ የምርምር፣ ቴክኖሎጂና ሽግግር ካውንስል ከዘርፉ አምራች ኢንዱስትሪ፣ የመንግስት ተቋማት፣ ዩኒቨርስቲዎች የተውጣጣ ካውንስል የማቋቋም፣ ኢንዱስትሪዎችን ወደ ክልሉ ለመሳብ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማብቃት እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ አንቱ የተባሉ አቅም የሚሆኑ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የቴክኖሎጂ ፓርኮች እንዲቋቋሙ የማድረግ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ቢሮዎች/መሥሪያ ቤቶች የምርምር ውጤቶችን ወደ ኢንዱስትሪና ወደ ገበያ ለማሸጋገር በማመቻቸት በአካዳሚክ እና በኢንዱስትሪ መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት፣ የእውቀት፣ የቴክኖሎጂ እና የባለሙያዎችን ሽግግር ለማፋጠን የሚያስችል ተቋም እንዲቋቋም ተገቢዉን ጥናት በማድረግ እንዲቋቋም የማድረግ ስራን ያጠቃልላል | | | | | | | | | | | | |
| 5.2.1 | የዘርፉን የጥናትና ምርምር፣ የቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀትና መተግበር | | ሰነድ | | 1 | | አኢልኢ | | | | | ## | ### | ### |
| 5.2.2 | የምርምርና የቴክኖሎጂ ተግባራትን በበላይነት የሚመራ ካውንስል ማቋቋምና ወደ ስራ ማስገባት | | በቁጥር | 1 | | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር ማኔጅመንት፣ አኢልኢ | መደበኛ በጀትና | **0.500** | | | ## | ### | ### |
| 5.2.3 | የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፓርኮች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ማድረግ | | በቁጥር | | | 1 | አኢልኢ | አጋር የልማት ድጋጅት ድጋፍ | | 200 | 340 | # | ### | ### |
| | **ግብ 5.3 ለኢመርጂንግ ቴክኖሎጂና ለኢንዱስትሪ 4.0 አብዮት መሠረት መጣል** | ከኢንደስትሪ 4.0 አብዮት እና አጠቃሊይ ዲጂታሊይዜሽ የዝግጁነት ዲሰሳ ጋር በተያያዘ ስራውን የሚመራ ስትሪንግ ኮሚቴና ቴክኒካል ስራዎችን የሚያከናውን ግብረ-ሀይል ማቋቋም፣ መልካም ተሞክሮዋችን፣ ፖሉሲና ስትራቴጂና የህግ ማዕቀፎችን ለስራው | | | | | | | | | | | | |
| 5.3.1 | አሠራር ስርዓትና አደረጃጀት መፍጠር | | ሰነድ | | 1 | | ኢንዱስትሪ ሚ/ር | አጋር ልማት | | **1** | | ## | ### | ### |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ጉዳይ፣ ስትራቴጂክ ግብና ዋና ዋና ተግባራት | የስትራቴጂክ ግብ መግለጫ | መለኪያ | የሚከናወንበት ጊዜ | | | የሚያከናውነው አካል | በጀት / የበጀት ምንጭ | በጀት በሚሊየን ብር | | | የመተግበር ዕድል | ያለው ጠቀሜታ | ተፅእኖ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | 2016 | 2017 | 2018 | | | |
| | | በሚጠቅም መልኩ የዳሰሳ ስራና የማፅቀፍ ጥናት፣ በማፅቀፍ ጥናቱ ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ እና ሃገራዊ ፍኖተ ካርታ የማዘጋጀት ስራን ያጠቃልላል | | | | | (ማኔጅመንት፣ ኢትዮጵያ ታምርት) | ድርጅት ድጋፍ | | | | | | |
| 5.3.2 | ከኢንዱስትሪ 4.0 አብዮት እና አጠቃላይ ዲጂታላይዜሽን ዳሰሳ ስራ ማከናወን | | ሰነድ | | 1 | | | | | 5 | 50 | # | ### | ### |
| 5.3.3 | የኢንዱስትሪ 4.0 እና ዲጂታላይዜሽን ሀገራዊ ፍኖተ-ካርታ ማዘጋጀት | | ሰነድ | | | 1 | | | | | | # | ### | ### |

ማስታወሻ፡ 17ቱን ስትራቴጂክ ግቦች ለማሳካት የተለዩ ዋና ዋና ተግባራት የመተግበር ዕድላቸውና ስትራቴጂውን ወደ ትግበራ በመስገባት ያላቸው ጠቀሜታና ተፅእኖ ደረጃ ለመለየት በዝርዝር በሠንጠረዥ የቀረበውን በሚከተለው ምልክቶች ያሉበትን ደረጃ ለማመላከት ተሞክራል።

**መካከለኛ-------# ከፍተኛ--------## በጣም ከፍተኛ------###**

## 3. ስጋቶችና የስጋት ማስወገጃ ስልቶች

ስጋቶች (Threats, Vulnerabilities and Risks) ፦ የአቅም ግንባታ ስተርራቴጂውን ውጤታማነት ሊያደናቅፉ የሚችሉና የታቀዱ ግቦች እንዳይሳኩ የሚያደርጉ ክስተቶች ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ስጋቶች ከመከሰታቸው በፊት የመከላከል ስትራቴጂ ለመንደፍና የሚያስከትሉትን አደጋ ለመቀነስ ሊያጋጥሙ የሚችሉትን መለየት ይገባል። ከዚህ አንጻር የአቅም ግንባታ ሥትራቴጂክ ዕቅዱን ስኬታማነት ሊፈታተኑ ይችላሉ ተብለው የተለዩ ስጋቶችና የማስወገጃ ስልቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 3.1. ስጋቶች

1. መንግስት ተገቢውን በጀት ካልፈቀደ እና የሥልጠና፣ የምርምር፣ የላቦራቶሪ፣ የወርክሾፕ ፋሲሊቲዎች ማሟላት ካልተቻለ በአቅም ግንባታው ውጤታማነትና የኢንዱስትሪ ድጋፍ ላይ ተፅዕኖው ከፍተኛ መሆኑ፤
2. የአምራች ኢንዱስትሪው ምርትና ምርታማነት አለመሻሻል፡- የአምራች ኢንዱስትሪው አቅም በሚፈለገው ደረጃ እንዲለማና እና ተወዳዳሪ እንዲሆን የራሱ ምርትና ምርታማነት ማደግ አለበት ይህ ሲሆን ተጨማሪ ተግባራትን ለማከናወን ይችላል። ነገር ግን ውጤታማነቱ ላይ ችግር ካለ ለአቅም ግንባታ መሠረተ ልማት በጥራትና በሚፈለገው መጠን ለማሟላት እና የሰው ኃይል አቅም ግንባታን በዕቅድ ይዞ ያለመተግበር ሊከሰት ይችላል፤
3. ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች በዚህ ሰነድ የሚቀርበውን የአደረጃጀት፣ የመዋቅር እና የአሰራር ምክረ-ሃሳብ ተቀብሎ ትግበራ ላይ ካልዋለ እንደሃገር የታሰበውን ለማሳካት አዳጋች መሆን፤
4. የዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ያለው ልምድ አናሳ መሆን እና በተፈለገው ደረጃ ሽግግሩን ለማሳለጥ ዕውቀትና ክህሎት ለመቅሰም ካልተቻለ ተፅእኖ መፍጠሩ፤ አጥጋቢ ያልሆነ የሥራ ባህል እና የሰው ኃይል ጉዳይ
5. ሰራተኛው ለኢንዱስትሪ ያለው አመለካከትና የኢንዱስትሪ የስራ ባህል ለመላበስ አዝጋሚ መሆን፡- ለኢንዱስትሪው ዘርፍ እድገት መልካም የስራ ባህልና አመለካከት ትልቅ ሚና ይጫወታል። በአገራችን ያለው ሁኔታ በምርታማነቱ ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ያለው ደካማ

የስራ ባህል መኖሩን ያሳያል፡፡ በመሆኑም ሠራተኛ ኃይል ምርታማነት መጨመር እና የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድን ስኬታማ ለማድረግ በዚህ ረገድ የአመላከከት ለውጡ ካልመጣ የኢንዱስትሪውን ልማት ይጎዳል፡፡

6. ክልልች እና ከተማ መስተዳድሮች የአቅም ግንባታ ተግባራትን ከውጪ አካል ብቻ የመጠበቅ ሁኔታ የመፈጠር፤ በራሳቸው በጀት መድበው ሁኔታዎችን አመቻችተው መተግበር ያለመቻል፤
7. የከፍተኛ ትምህርት እና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ከዚህ በፊት በሚሄዱበት በተለመደው መንገድ ፕሮግራሞችን ለመተግበር የመንቀሳቀስ፤ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት በተባጭ ያለመፈፀም፤
8. የዓለም አቀፍ ሁኔታ በየጊዜው ተለዋዋጭ መሆን እንዲሁም የዓለም ኢኮኖሚ በየጊዜው መቀዛቀዝ የልማት አጋሮች እና ወዳጅ ሃገራት የሚሰጡት የቴክኒክ፣ ፋይናንስ እና የማቴሪያል ድጋፍ የሚቀንስ ከሆነ በሥታረተጂው ትግበራ ውጤት ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር መቻሉ፡፡

## 3.2. የስጋት ማስወገጃ ስልቶች

1. ለአምራች ኢንዱስትሪው ውጤታማነት የአቅም ግንባታ ስትራተጂን አስፈላጊነት በሰፊው ማስተዋወቅ እና የሥልጠና ፋሲሊቲዎችን ፣ የምርምር ፋሲሊቲዎችን፣ ላቦራቶሪዎችንና ወርክሾፖችን ማሟላት ወሳኝ መሆኑን ለአስፈፃሚው በማስገንዘብ መንግስት ተገቢውን በጀት እንዲፈቅድ ማድረግ እና እና ከልማት አጋሮች የፋይናንስ፣ የማቴሪያልና ቴክኒክ ድጋፍን ማፈላለግ፤
2. ለክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ተናባቢ የሆነ አወቃቀር፣ ዕቅድና ሪፖርትን አስፈላጊነት በከፍተኛ አመራር ደረጃ ግንዛቤ በመፍጠር ምክረሃሳቡን እንዲቀበሉት ጥረት የማድረግ፤
3. የዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ያለው ልምድን ለማሳደግ የሌሎች ሃገራትን ልምድ ቤንች ማርክ ማድረግ፣ በቁርኝት ምረሃ-ግብር እና በሌሎች የድጋፍ ማዕቀፎች ከውጪ ሊገኙ የሚችሉ የሰው ሃይል እና የቴክኒክ ድጋፍን በተክኖሎጂ ሽግግር እና ዕውቀት ሽግግር ላይ ሊረዱ የሚችሉ እንዲሆኑ ቅድሚያ ፍላጎትን ማሳወቅ፤በውጪ ሃገራት የሚሰጡ የስልጠና መርሃግብሮችን እና ልምድ ቀሰማዎችን ወደምንፈልገው ትኩረት እንዲደረግ በሃገር ደረጃ ውይይት ማድረግ፤ ኢንስቲትዩቶችን የቴክኖሎጂ እና ዕውቀት ሽግግር ማዕከል ለማድረግ አስፈላጊውን ፋሲሊቲ ማሟላት፤ በውጪ ቀጥታ

ኢንቨስትመንት የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን እና ባለሙያዎችን በመጠቀም ሽግግሩን ማሳለጥ፡፡

4. የአምራች ኢንዱስትሪ አቅም ግንባታ የሁሉም በክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች ሥራ መሆኑን በከፍተኛ አመራሩ ደረጃ መግባባት ላይ ለመድረስ ከመነሻው ጀምሮ መወያየት፣ አስተያየቶችን ማካተት እና እንደ ክልሉ ሁኔታ እንዲተገብሩ የማሳመን ሥራ መስራት፡፡
5. የኢንዱስትሪ የሥራ ባህልን በሚሰጡ ሥልጠናዎች ሁሉ ማካተት፣ በተለይ የኢንዱስትሪ ስልጠና መጀመሪያ አመለካከት መለወጥ ላይ ትኩረት በማድረግ መስራት እንዲሁም በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ ከሰራተኞች የሚጠበቅ የሥነ ምግባር ስታንዳርድ በማዘጋጀት መተግበር፡፡
6. የከፍተኛ ትምህርት እና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚቀረፁ ሙያ ደረጃዎች፣ የሚዘጋጁ የከፍተኛ ትምህርት ካሪኩለሞች ከኢንዱስትሪው ፍላጎት በመነሳት እና ከኢንዱስትሪው እና ሙያ ማህበራት ጋር በመሆን እንዲቀረፅ ሙያ ብቃት ምዘናው በኢንዱስትሪዎች እንዲሆን ማድረግ፤
7. የዓለም አቀፍ ተለዋዋጭነት የሚያመጣውን ተፅዕኖን ለመቀነስ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የመተንበይና የስትራቴጂካዊ አመራር አቅም በቀጣይነት በማሳደግ ለተለዋዋጭ ሁኔታው የሚመጥን ስልት በመንደፍ የተለያዩ አማራጮችን መጠቀም፡፡

## 4. ማስፈፀሚያ ስልቶችና የክትትልና ግምገማ ስርዓት

### 4.1. የማስፈጸሚያ ስልቶች

ከላይ የተቀመጡ ዓላማዎችንና ግቦች ለማሳካት የሚያስፈልጉ ሥልቶች እንደሚከተለው ተለይተዋል፡፡

- ውጤታማና ከወቅቱ የኢንዱስትሪ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም የአቅም ልማት ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽና ተግባራዊ በማድረግ በየደረጃው ያለውን አመራርና ባለሙያ አቅም በአጭር እና በረጅም ጊዜ ሥልጠና ማብቃት፤
- የጥናትና ምርምር፣ ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር፣ ሥልጠናና ማማከር ሥራዎችን በውጤታማነት ለማከናወንና የኢንዱስትሪውን ዘላቂ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ ብሎም በዘርፉ ልህቀት ለመፍጠር ተቋማዊ ፋሲሊቲዎችን፣ ላቦራቶሪዎችንና ወርክሾፖችን በመንግስት በጀትና በልማት አጋሮች ድጋፍ ማሟላት፤

- የኢንዱስትሪውን ምርት ጥራት፣ ምርታማነት፣ ተወዳዳሪነትና የሥራ ባህል ለማሳደግ የሚያስችል የከይዘን ሥልጠና እና ማማከር ድጋፍ ለኢንዱስትሪ አመራርና ባለሙያዎች ክፍተትን መሠረት ባደረገ መልኩ መስጠት፤
- የኢንዱስትሪ ድጋፍ ፓኬጆችን በመቅረጽና በማስተዋወቅ የኢንዱስትሪውን የመጠየቅ ፍላጎት እና ከምርምር ማዕከላት ያለውን ቅርርብ በማሻሻል የሁለትዮሽ ትብብሮችን መመሥረትና የድጋፍ ሥራዎችን ውጤታማ ማድረግ፤ አምራች ኢንዱስትሪው ውጤትንና አፈጻጸምን መሠረት ያደረገ የማበረታቻና ዕውቅና ሥርዓቶችን በመዘርጋት እንዲተገበር ማድረግ፤
- ከከፍተኛ ትምህርት፣ የስልጠና ተቋማት እና ሌሎች የምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅት በመፍጠር በኢንዱስትሪው ፍላጎት መሰረት የዘርፉን የሰው ኃይል እንዲለማ ማድረግ እና የምርምርና ቴክኖሎጂ ሥርጸትን ውጤታማ ለማድረግ የተቀናጀ አቅም በመፍጠር መሠረተ ልማቶችን በሙሉ አቅም መጠቀም፤
- የዘርፉን ሥራዎች፣ የሚሰጡ የኢንዱስትሪ ድጋፍ፣ በኢንስቲትዩቱና በማዕከላት መካከል ያለውን ቅንጅት በላቀና በወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ለማከናወንና አፈጻጸምን ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ዘመናዊ አሰራሮችን መተግበር እና የኢ.ኮ.ቴ. አጠቃቀምን በማሳደግ አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ማድረግ፤
- ቴክኖሎጂ ማሻሻያ በአለም አቀፍ ደራጃ ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ምርጥ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማምጣት፣ ማላመድና ማሻጋገር፤ዲጂታል ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሠራር ማሻሻያ መተግበር፤ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ ውስጣዊ አሰራር፣ ውጫዊ ቅንጅት፣ እና አገልግሎት አሰጣጥ ማዘመን፤
- የአቅም ልማቱን የሚያግዙ የተለያዩ የአሠራር ስርዓቶችና ማሻሻያ ማለትም የመዋቅርና አደረጃጀት ማሻሻያ፣ የሙያ ብቃትና የማህበራት የስራ ፍቃድ ማረጋገጫ ስርዓት ሰነድ ዝግጅት፣ የክልሎች ልዩ ድጋፍ ማዕቀፍ፣የእውቅናና ማበረታቻ ስርዓት፣የሙያ ስነምግባር ማስጠበቂያ ስርዓት፣የውስጥ ሀብትን በአግባቡ መጠቅም የሚያስችሉ ስርዓቶች፣ የአገልግሎቶ ስታንዳርድ ዝግጅት፣የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ከአጋር አካላት ጋር የሚኖር የትብብር ስርዓት በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግ፤

## 4.2. የክትትልና ግምገማ ስርዓት

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሠጠውን ሀገራዊ ተልዕኮ ለማሳካት ከነደፋቸው ስትራተጂዎች ውስጥ የአቅም ልማት ስትራተጂ አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ስትራቴጂክ ዕቅዱን ውጤት በሚያመጣ መልኩ ለመምራትና ለማስፈጸም የሚከተሉትን የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶች ቀርጿል፡፡

- የአቅም ልማት ስትራቴጂው ቁልፍ የውጤት አመላካቾች (key performance indicators) መቅረጽና ተግባራቱን ሌሎች ተያያዥ ከሆኑ ተግባራት ጋር በማገናኘት እስከ ግለሰብ ድረስ የሚከናወኑ ሥራዎች ቁልፍ ተብሎ የተቀመጠውን ውጤት ስለማሳካታቸው ይታያል፡፡

- የአፈጻጸም ደረጃንና የተገኙ ውጤቶችን ለመለካትና ተዓማኒነትን ለማሳደግ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት የሚዘረጋ ሲሆን የመረጃዎች ትክክለኝነትና ጥራት በቀላሉ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡ ከዚህም ባለፈ አፈጻጸሞችንና መረጃዎች ለባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ የሚደረጉ ሲሆን ቀልጣፋ የመረጃ ቅብብሎሽን በመፍጠር ትስስሩ በተሻለ ሁኔታ እንዲፈጥሩ ለማስቻል ጥረት ይደረጋል፡፡

- ሥራዎችን ከሪፖርት ባለፈ በመስክ ጉብኝትና ምልከታ የታገዘ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማከናወን የተግባራትን የአፈጻጸም ደረጃ ከመለካት ባለፈ የገጽ ለገጽ ውይይትና የሥራ ቦታ ምልከታ ዕድል ስለሚኖረው የሥራ ተነሳሽነትን የሚፈጥር ይሆናል፡፡ ስለሆነም ወቅቱን በጠበቀ እና በተቃደ መልኩ እንደ አስፈላጊነቱ በተለያዩ ቦታዎች የመስክ ጉብኝትና ምልከታ ይከናወናል፡፡

- የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት የሚመጥን፣ የታቀደ እና ወቅታዊ የሆነ የዕቅድ ትውውቅ እና አፈጻጸም ግምገማ ውይይት የሚከናወን ሲሆን ይህም በዋናው ዕቅድ ውስጥ ተካቶ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

### 4.2.1. የክትትልና ግምገማ መርሀ ግብር

ክትትልና ግምገማ መርሃ ግብር መደበኛ ዕቅድ ግምገማ በሚደረግበት ጊዜ ተቀናጅቶ የአቅም ልማት አተገባበሩ እራሱን ችሎ የሚቀርብ ሲሆን፤ መርሃ ግብሩ በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡
:

| ሥልት | ዓላማ | ጊዜ | ተሳታፊዎች |
| --- | --- | --- | --- |
| ከተቋማዊ የሩብ ዓመት፣ የ6 ወር እና የዓመት ክትትልና ግምገማ ጋር በማስተሳሰር የሚደረግ | በዕቅድ መሠረት የተከናወኑ ሥራዎችና የተደረሰበት ደረጃ መከታተል፣ መደገፍ እና አፈጻጸሙን መለካት | በ3 ወር፣ በ6 ወር እና በየዓመቱ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አመራሮችና ሰራተኞች፣ ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች፣ ተጠሪ ተቋማት፣ ባለድርሻ አካላት፣ |
| የባለድርሻ አካላት ውይይት | የዕቅድ ገለጻ፣ የአፈጻጸም ግምገማ፣የአቅም ልማት ስልጠና፣ የጥናትና ምርምር ውጤቶች እና ሌሎች የጋራ ሥራዎች ላይ ለመምከር | በየ6 ወር | በስትራቴጂክ ዕቅዱ የተለዩ ሁሉም ባለድርሻ እና ተባባሪ አካላት |
| *የመስክ ጉብኝትና ምልከታ* | ሥራዎችን ከሪፖርት ባለፈ በአካል ለመከታተልና ለመደገፍ | በየ6 ወር | የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች የዘርፍና ሙያ ማህበራት፣ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላት እና ሌሎችም የሚመለከታቸው እንደአስፈላጊነቱ ይሳተፋሉ፤ |
| የሥትራተጂው ትግበራ አጋማሽ ግምገማ (mid-term review) | በስትራተጂክ ዕቅዱ አጋማሽ የተገኙ ውጤቶችንና ስኬቶችን ለመገምገም እንዲሁም ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በመለየት መፍትሄ ለመስጠት እና አፈጻጸሙን መነሻ በማድረግ ዕቅዱን ክለሳ ማካሄድ፤ | በ1 ዓመት ከግማሽ | የሥትራቴጂክ ጉዳዮች እና የሰው ሃብት ሥራ አስፈጻሚ ፣ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር፤ |
| የሥትራተጂው ዕቅድ ትግበራ ዘመን ማጠናቀቂያ ግምገማ (final evaluation) | በዕቅድ መሠረት በልማት ዘመኑ የተገኙ ስኬቶችንና ፋይዳ የሚገመገም ሲሆን እንደማጠቃለያ ግምገማ የኢኮኖሚያዊ ሽግግር ስለመሳካቱ ይታያል፤ አፈጻጸሙን በጥናት ላይ በመመስረት በዝርዝር በመገምገም ለቀጣይ የልማት ዕቅዶች ቁልፍ የፖሊሲና ስትራቴጂ ግብዓቶችን መለየት፤ | በ3 ዓመት | የሥትራቴጂክ ጉዳዮች እና የሰው ሃብት ሥራ አስፈጻሚ ፣ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር፤ |

## አባሪ አንድ፡- ስትራቴጂክ ኢኒሼቲቮች

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ኢኒሺዬቲቭ | መግለጫና ወሰን | የሚጠበቅ ውጤት | ከኢንሺዬቲቩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያስፈልገው ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | አስፈጻሚ አካል | የትኩረት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የአሠራር ስርዓቶችን መዘርጋት | **መግለጫ**<br>የባለድርሻ አካላት አመራርን ግንዛቤ መፍጠሪያ፣ የቢዝነስ ልማት አገልግሎትን (BDS) ተደራሽ ለማድረግ፣ ከአጋር አካላት ጋር የሚኖር ትብብርን ለማሳለጥ፣ የመንግስት የኢንዱስትሪ ደጋፊ ተቋማት የሰው ሀብት ልማትን ለመምራት፣ የአምራች ኢንዱስትሪውን የሰው ሀብት አቅም ሊያጎለብት የሚችል የስልጠና ተደራሽነትን ለማስፋት እና ለአምራች ኢንዱስትሪው በአቅም ልማት ዙሪያ በተሰጡ አገልግሎቶች የተገኙ ውጤቶችን ለማዝለቅ የሚያስችሉ የአሠራር ስርዓቶች በቅድሚያ ተሰጥቷቸው ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው፡፡ | የተዘረጉ የአሠራር ስርዓቶች | | 1. ከሚመለከታቸው አካላት በተውጣጣ ቡድን የአሠራር ስርዓቱን ማዘጋጀት<br>2. ከሁሉም ክልልና የከተማ መስተዳድሮች እንዲሁም ከፌደራል ተቋማት የተወጣጡ የዘርፉ ባለሙያዎችን የአሠራር ስርዓቱ ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡<br>3.የአሠራር ስርዓቱን ወደ ትግበራ ማስገባት | በ6ወር | በመደበኛ በጀት የሚሸፈን | ኢንዱስትሪ ሚንስቴር | የመጀመሪያ ደረጃ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ኢኒሺዬቲቭ | መግለጫና ወሰን | የሚጠበቅ ውጤት | ከኢንሺዬቲቩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያስፈልገው ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | አስፈጻሚ አካል | የትኩረት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | **ወሰን፡**<br>ከፌደራል እስከ ወረዳና ከተማ መስተዳድር የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ የሚደግፉ የመንግስት ተቋማት እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪው የሚያካትት ይሆናል፡፡ | | | | | | | |
| 2. | **የመዋቅርና አደረጃጀት ማሻሻያ** | **መግለጫ፡**<br>በዘርፉ አሁን ላይ የሚታየውን ወጥ ያለመሆንና ተናባቢነት እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራሩ የላላውን መዋቅራዊ አደረጃጀት ማሻሻል አስፈልጓል፡፡ በመሆኑም ከፌደራል አንስቶ እስከ ክልልና የከተማ መስተዳድሮች ተዋረዱንና ፌደራላዊ ስርዓቱን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ወደ ኢኑዱስትሪያላይዜሽን የኢኮኖሚ ማዋቅራዊ ሽግግር ሊያሳካ የሚችል መዋቅራዊ አደረጃጀት አሻሽሎ መተግበር ያስፈልጋል፡፡<br>**ወሰን፡** | ለሚመለከተው አካል ቀርቦ የጸደቀ የመዋቅር አደረጃጀት ሰነድ | **ስትራቴጂክ ጉዳይ 1፡** ኢንዱስትሪያላይዜሽንን በተሟላ፣ ሁለንተናዊና የጋራ ተቋማዊ አቅም አለመመራቱ | 1. ከሁሉም ክልልና የከተማ መስተዳድሮች እንዲሁም ከፌደራል ተቋማት የተወጣጡ የዘርፉ ባለሙያዎችን ያካተተ ኮሚቴ ማዋቀር፡፡<br>2. የድርጊት መርሀ-ግብር በማዘጋጀት አስፈላጊውን በጀት ማስፈቀድ፡፡<br>3. ሰነዱን በታቀደለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ማከናወን፡፡<br>4. በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ከሚመለከታቸው የበላይ አመራሮች፣ባለድርሻዎችና ባለሙያዎች ጋር የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ለሰነዱን ሚያዳብሩ ግብረመልሶችን መሰብሰብ፡፡ | 6 ወር | በመደበኛ በጀት የሚሸፈን | ኢንዱስትሪ ሚንስቴር | የመጀመሪያ ደረጃ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ኢኒሺዬቲቭ | መግለጫና ወሰን | የሚጠበቅ ውጤት | ከኢንሺዬቲቩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያስፈልገው ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | አስፈጻሚ አካል | የትኩረት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በፌደራል፣በክልልና የከተማ መስተዳድሮች አምራች ኢንዱስትሪውን በሚደግፉና በሚቆጣጠሩ ተቋማት ላይ የሚተገበር፡፡ | | | 5. ከግብረመልሶቹ መነሻነት የመጨረሻውን ሰነድ አዳብሮና አስተካክሎ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ማጸደቅ፡፡ | | | | |
| 3. | የሙያ ብቃትና የማህበራት የስራ ፍቃድ ማረጋገጫ ስርዓት ሰነድ ዝግጅት | **መግለጫ፡**<br>በአምራች ኢንዱስትሪ ዙሪያ ተቀጥረዉ ለሚሰሩ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግስት ፣ የኢንዱስትሪውና የግል ባለሙያዎች በየጊዜው የሙያ ብቃታቸውን በመመዘንና በማረጋገጥ የብቃት ሰርተፊኬት የሚገኙበትን ስርዓት መዘርጋት፡ ዘርፉ ዙሪያ የሚሰሩ ማህበራት ለዘርፉ እድገት በሚፈለገ ልክ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ንዲያበረክቱ ሚያስችል የማህበራት የስራ ፋቃድ አሰጣጥና እድሳት ስርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፡<br>**ወሰን፡**<br>በደረጃው ላሉ ሁሉም የዘርፉ የመንግስትና የግል ባለሙያዎች ላይ የማህበራት ፍቃድ፡ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ዙሪያ ህጋዊ ሰውነት | 1. የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ስርዓት ሰነድ<br>2. የማህበራት የስራ ፍቃድ ሰነድ | **ስትራቴጂክ ጉዳይ 5፡** ለኢንዱስትሪው የሚሰጡ የአቅም ልማትየአገልግሎት ድጋፍ መዓቀፎች ውጤታማና ዘላቂ ያለመሆን | 1. ከትምህርት ሚንስቴር፣ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ከስራና ክህሎት፣እንዲሁም ከተለያዮ የፌደራል ተቋማት የተወጣጡ የዘርፉ ባለሙያዎችን ያካተተ ኮሚቴ ማዋቀር፡፡<br>2. የድርጊት መርሀ-ግብር በማዘጋጀት አስፈላጊውን በጀት ማስፈቀድ፡፡<br>3. ሰነዱን በታቀደለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ማከናወን፡፡<br>4. በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ከሚመለከታቸው የበላይ አመራሮች፣ባለድርሻዎችና ባለሙያዎች ጋር የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ለሰነዱን ሚያዳብሩ ግብረመልሶችን መሰብሰብ፡፡<br>5. ከግብረመልሶቹ መነሻነት የመጨረሻውን ሰነድ አዳብሮና | 6 ወር | በመደበኛ በጀት የሚሸፈን | ኢንዱስትሪ ሚንስቴር | ሁለተኛ ደረጃ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ኢኒሺዬቲቭ | መግለጫና ወሰን | የሚጠበቅ ውጤት | ከኢንሺዬቲቩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያስፈልገው ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | አስፈጻሚ አካል | የትኩረት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አግኝተውና ተመዝግበው በሚሰሩ ማህበራት ላይ የሚተገበር ይሆናለ | | | አስተካክሎ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ማጸደቅ፡፡ | | | | |
| 4. | የክልሎች ልዩ ድጋፍ ማዕቀፍ | **መግለጫ፡**<br>በኢንዱስትሪያላይዜሽን እድገት በአንጻራዊነት ወደኋላ የቀሩ ክልሎችን ልዩ ድጋፍ በመስጠት እንደ ሀገር በዘርፉ የተመጣተነ እድገትን ከማረጋገጥ አኳያ ልዩ የአቅም ልማትላይ የሚያተኩር የአሰራር መዓቀፍ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡<br>**ወሰን፡**<br>የልዩ ድጋፍ ማዕቀፉ የሚመለከታቸው ክልሎች፡ ሱማሌ፣አፋር፣ቤንሻንጉል፣ ጋንቤላ፣ደቡብ ምዕራብ እና ትግራይ ይሆናሉ<br>ልዩ ድጋፉ በዋናነት የዘርፉን የሰው ሀይል በየደረጃው በማሰልጠንና በማብቃት ላይ ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል፡፡ | በሚመለከተው አካል የጸደቀ የክልሎች ልዩ ድጋፍ ማዕቀፍ ሰነድ | **ስትራቴጂክ ጉዳይ 2፡** የዘርፉ መንግስታዊ ተቋማት የሰው ሀብት የአቅም ልማትና ልማት ደካማ መሆን | 1. ልዩ ድጋፉ ከሚመለከታቸው ክልሎች እና ከፌደራል ተቋማት የተወጣጡ የዘርፉ ባለሙያዎችን ያካተተ ኮሚቴ ማዋቀር፡፡<br>2. የድርጊት መርሀ-ግብር በማዘጋጀት አስፈላጊውን በጀት ማስፈቀድ፡፡<br>3. ሰነዱን በታቀደለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ማከናወን፡፡<br>4. በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ከሚመለከታቸው የበላይ አመራሮች፣ባለድርሻዎችና ባለሙያዎች ጋር የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ለሰነዱን ሚያዳብሩ ግብረመልሶችን መሰብሰብ፡፡<br>5. ከግብረመልሶቹ መነሻነት የመጨረሻውን ሰነድ አዳብሮና አስተካክሎ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ማጸደቅ፡፡ | 3 ወር | በመደበኛ በጀት የሚሸፈን | ኢንዱስትሪ ሚንስቴር | ሁለተኛ ደረጃ |
| 5. | የእውቅናና ማበረታቻ ስርዓት | **መግለጫ፡**<br>በኢንዱስትሪያላይዜሽን የሚመዘገበውን የተሻለ ውጤት ቀጣይነት ለማረጋገጥ | በሚመለከተው አካል የጸደቁ | **ስትራቴጂክ ጉዳይ 5፡** ለኢንዱስትሪው የሚሰጡ የአቅም ልማትየአገልግሎት | 1. ከሁሉም ክልልና የከተማ መስተዳድሮች እንዲሁም ከፌደራል ተቋማት የተወጣጡ | 3 ወር | በመደበኛ በጀት የሚሸፈን | ኢንዱስትሪ ሚንስቴር | ሁለተኛ ደረጃ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ኢኒሺዬቲቭ | መግለጫና ወሰን | የሚጠበቅ ውጤት | ከኢንሺዬቲቩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያስፈልገው ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | አስፈጻሚ አካል | የትኩረት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከሚያስችሉ ስልቶች ዋነኛው በዘርፉ ጉልህ ሚና ያላቸውንና የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ አካላትን በየጊዜው ማመስገንና እውቅና መስጠት አንዱ ነው፡፡<br>**ወሰን፡**<br>የእውቅናና ማበረታቻ ስርዓቱ የባለድርሻ አካላትን አስተዋጽዖና ባህሪ ባገናዘበ መልኩ በሚከተሉት ክፍሎች ተከፍሎ መታየት ይኖርበታል፡፡<br>1. በመንግት ተቋማት ኢንዱስትሪውን ለሚደግፉ አመራሮችና ባለሙያዎችን<br>2. በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሰሩ አመራሮች፣ ቡድኖች፣ሰራተኞች እና በለሀብቶችን<br>3. ለአምራች ኢንዱስትሪው ድጋፍ የሚሰጡ የባለድርሻ አካላት አመራሮችና ሰራተኞች<br>4. ከትምህርት ተቋማት በየደረጃው ለኢንዱስትሪ እድገት አስተዋጽዖ የሚያበረክቱ | 1. ለኢንዱስትሪው ድጋፍ የሚሰጡበ በየደረጃው ላሉ የመንግስት ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች የእውቅናና ማበረታቻ ስርዓት ሰነድ<br>2. በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሰሩ አመራሮች፣ቡድኖች፣ ሰራተኞች እና ባለሀብቶች የእውቅናና ማበረታቻ ስርዓት ሰነድ<br>3. ለአምራች ኢንዱስትሪው ድጋፍ የሚሰጡ የባለድርሻ አካላት አመራሮችና ሰራተኞች የእውቅናና ማበረታቻ ስርዓት ሰነድ<br>4. ለኢንዱስትሪው እድገት አስተዋጽዖ የሚያበረክቱ ተመራማሪዎች፣ መምህራን ፣ ተማሪዎች እና | ድጋፍ መዓቀፎች ውጤታማና ዘላቂ ያለመሆን<br><br>**ስትራቴጂክ ጉዳይ 1፡** ኢንዱስትሪያላይዜሽንን በተሟላ፤ ሁለንተናዊና የጋራ ተቋማዊ አቅም አለመመራቱ | የዘርፉ ባለሙያዎችን ያካተተ ኮሚቴ ማዋቀር፡፡<br>2. የድርጊት መርሀ-ግብር በማዘጋጀት አስፈላጊውን በጀት ማስፈቀድ፡፡<br>3. ሰነዱን በታቀደለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ማከናወን፡፡<br>4. በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ከሚመለከታቸው የበላይ አመራሮች፣ባለድርሻዎችና ባለሙያዎች ጋር የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ለሰነዱን ሚያዳብሩ ግብረመልሶችን መሰብሰብ፡፡<br>5. ከግብረመልሶቹ መነሻነት የመጨረሻውን ሰነድ አዳብሮና አስተካክሎ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ማጸደቅ፡፡<br>1. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት የተወጣጡ የዘርፉ ባለሙያዎችን ያካተተ ኮሚቴ ማዋቀር፡፡<br>2. የድርጊት መርሀ-ግብር በማዘጋጀት አስፈላጊውን በጀት ማስፈቀድ፡፡<br>3. ሰነዱን በታቀደለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ማከናወን፡፡ | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ኢኒሺዬቲቭ | መግለጫና ወሰን | የሚጠበቅ ውጤት | ከኢንሺዬቲቡ ጋር ግንኙነት ያላቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያስፈልገው ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | አስፈጻሚ አካል | የትኩረት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ተመራማሪዎች፣መምህራን እና ተማሪዎች | በየደረጃው ለሚገኙ የትምህርትና ምርምር ተቋማት የእውቅናና ማበረታቻ ስርዓት ሰነድ | | 4. በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ከሚመለከታቸው የበላይ አመራሮች፣ባለድርሻዎችና ባለሙያዎች ጋር የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ለሰነዱን ሚያዳብሩ ግብረመልሶችን መሰብሰብ፡፡ | | | | |
| 6. | የሙያ ስነምግባር ማስጠበቂያ ስርዓት | **መግለጫ:**<br>በየደረጃው ባሉ መንግስት ተቋማት የሚያገለግሉ አመራሮችን ባለሙያዎች ከሙያው፣ኢንዱስትሪውና ህብረተሰቡ ከሚጠብቃቸው ስነምግባሮች አንጻር ወጥነት ያለውና ሊተገበር የሚችል የሙያ ስነምግባር ስርዓት መዘርጋት አስፈልጓል፡፡<br>**ወሰን:**<br>በዘርፉ ሁሉም መንግስታዊ ተቋማት ባሉ አመራርና ሰራተኞች የሚተገበር | 1. በሚመለከተው አካል የጸደቀ የሙያ ስነምግባር ማስጠበቂያ ሰነድ | **ስትራቴጂክ ጉዳይ 2:** የዘርፉ መንግስታዊ ተቋማት የሰው ሀብት የአቅም ልማትና ልማት ደካማ መሆን | 6. ከግብረመልሶቹ መነሻነት የመጨረሻውን ሰነድ አዳብሮና አስተካክሎ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ማጸደቅ፡፡ | 3 ወር | በመደበኛ በጀት የሚሸፈን | ኢንዱስትሪ ሚንስቴር | ሦስተኛ ደረጃ |
| 7. | የውስጥ ሀብትን በአግባቡ መጠቅም የሚያስችሉ ስርዓቶች | **መግለጫ:**<br>በተለይ የዘርፉ መንግስታዊ ተቋማት ያላቸውን የውስጥ አቅም ተጠቅመው ገቢን እንዲያመነጩ እና እንዲጠቀሙ | በሚመለከተው አካል የጸደቀ<br>2. የውስጥ ገቢን ማመንጨትና መጠቀም የሚያስችል የህግ መዓቀፍ ሰነድ | ስትራቴጂክ ጉዳይ 4: የመሰረተ ሌማትና ቁሳዊ ሀብት አቅምና አጠቃቀም ውስንነት | | 3 ወር | በመደበኛ በጀት የሚሸፈን | ኢንዱስትሪ ሚንስቴር | ሁለተኛ ደረጃ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ኢኒሺዬቲቭ | ማግለጫና ወሰን | የሚጠበቅ ውጤት | ከኢንሺዬቲቩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያስፈልገው ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | አስፈጻሚ አካል | የትኩረት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ አስፈልጓል፡፡<br><br>ከዚህ በተጨማሪም ወጥ የሆነና የተደራጀ ምቹ የስራ ቦታን ለመፍጠር እንዲሁም የተፈጠረውን ሁኔታ አስጠብቆ ለማዝለቅ የሚያስችል የስራ ቦታ ስታንዳርድ በሁሉም የዘርፉ መንግስታዊ ተቋማት መተግበር ያስፈልጋል፡፡<br>ቁሳዊ ሀብቶችን በተመለከተ ያሉትን ሀብቶች በአግባቡ ጠብቆና ተንከባክቦ በጋራ ለመጠቀም በሚያስችል መልኩ ያለውን የንብረት አስተዳደር መመሪያ ማሻሻል ይጠይቃል፡፡<br>**ውሰን፡**<br>የውስጥ ገቢን ማመንጨትና መጠቀምን በተመለከተበፌደራል ደረጃ በዋናነት በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ስር የሚገኙትን ስድስት ማዓከላት ታሳቢ ያደረገ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የዘርፉ መንግስታዊ | 3. የስራ ቦታ ስታንዳርድ ሰነድ<br>4. የተሻሻለ የንብረት አስተዳደር ሰነድ | | | | | | |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ኢኒሺዬቲቭ | መግለጫና ወሰን | የሚጠበቅ ውጤት | ከኢንሺዬቲቩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያስፈልገው ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | አስፈጻሚ አካል | የትኩረት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ተቋማት በሂደት ሊተገበር ይችላል።<br><br>የስራ ቦታ ስታንዳርድ እና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎች ከፌደራል እስከ ክልልና ከተሞች ባሉ ሁሉም የዘርፉ መንግስታዊ ተቋማት የሚተገበሩ ይሆናል። | | | | | | | |
| 8. | የአገልግሎቶ ስታንዳርድ ዝግጅት | **መግለጫ:**<br>ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በመንግስት ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶች ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጤታ ለማድረግ የሚያስችል የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ በማስቀመጥ አገልገሎቱን ተደራሽ ማድረግ የሚጠበቅ ይሆናል።<br><br>**ወሰን:**<br>አምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለመደገፍ በመንግስት ከፌደራል እስከ ወረዳና ከተማ መስተዳድሮች የተዘረጉ መዋቅሮችን የሚያካትት ይሆናል፡ | 1. የስልጠና አገልግሎት ስርዓትና ፓኬጆች ሰነድ<br>2. የማማከር አገልግሎት ስርዓትና ፓኬጆች ሰነድ<br>3. የኢንተርፕራይዞች የስልጠናና ማማከር ድጋፍ አገልግሎት ስርዓትሰነድ<br>4. የጥናትና ምርምር ስርዓት ሰነድ<br>5. የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ሰነድ | | 1. በፌደራልና በክልል የሚሰጡ አገልግሎቶችን ስታንዳርዶች ማዘጋጀት<br>2. የስልጠና አገልግሎት ፓኬጆችን ማዘጋጀት<br>3. የማማከር አገልግሎት ስርዓት ፓኬጆችን ማዘጋጀት<br>4. የኢንተርፕራይዞች የስልጠናና ማማከር ድጋፍ አገልግሎት ስርዓትሰነድ ማዘጋጀት<br>5. የጥናትና ምርምር ስርዓት ሰነድ ማዘጋጀት | በ6ወር | በመደበኛ በጀት የሚሸፈን | ኢንዱስትሪ ሚንስቴር ፣ ክልሎች፣ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቱትዩት፣ የኢትዮጵያ ኢንተር ፕራይዝ ልማት | ሁለተኛ ደረጃ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ኢኒሺዬቲቭ | መግለጫና ወሰን | የሚጠበቅ ውጤት | ከኢንሺዬቲቩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያስፈልገው ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | አስፈጻሚ አካል | የትኩረት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9. | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም | **መግለጫ:**<br>ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ለማሳደግ በዘርፉ አስፈጻሚ ተቋማትና በኢንዱስትሪው ውስጥ መረጃን ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ እንዲሁም ቴክኖሎጂው ለኢንዱስትሪው የሚያደርገውን አስተዋፅኦ በማሳደግ የሚጠበቅ ይሆናል<br><br>**ወሰን፡**<br>ከፌደራል እስከ ወረዳ ና ከተማ መስተዳድር የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ የሚደግፉ የመንግስት ተቋማት እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪው የሚያትት ይሆናል፡፡ | 1.የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ የሚደግፉ አካላት የተቀላጠፈ የመረጃ አያያዥና የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መፍጠር<br><br>2.የአምራች ኢንዱስትሪው የተገነባ የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት<br><br>3አምራች ኢንዱስትሪው .የቴክኖሎጅ ስርዓትን ለገበያ መደራሻ እና የግብይት ስርዓት እንዲውል ማስቻል፡፡ | | 1.ከሁሉም ክልልና የከተማ መስተዳድሮች እንዲሁም ከፌደራል ተቋማት የተወጣጡ የዘርፉ ባለሙያዎችን ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡<br><br>2.በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ከሚመለከታቸው የበላይ አመራሮች፣ ባለድርሻዎችና ባለሙያዎች ጋር የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡<br><br>3.የተሻለ ተሞክሮ ያላቸውን አካላት ልምድ እንዲቀሰምባቸው መለየት<br><br>4.የተሻለ ልምድ ያላቸውን ተቋማት ልምዳቸውን እንዲያጋሩ ማድረግ | በ6ወር | በመደበኛ በጀት የሚሸፈን | ኢንዱስትሪ ሚንስቴር ፣ ክልሎች፣ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቱትዩት፣ የኢትዮጵያ ኢንተር ፕራይዝ ልማት | ሁለተኛ ደረጃ |
| 10 | ከአጋር አካላት ጋር የሚኖር የትብብር ስርዓት | **መግለጫ**<br><br>የአምራች ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ በመንግስት የሚደረገው ድጋፍ ብቻ በቂ ባለመሆኑ ከአጋር ድርጅቶች ጋር ትብብር በመፈጠር እገዛ የሚያደርጉበትን ስርኣት | 1.ለአምራች ኢንዱስትሪው ድጋፍ የሚደረግባቸውን የትኩረት መስኮች መለየት<br><br>2.ድጋፍ የሚያደርጉ አጋር አካለትን መለየት | | 1.የአጋር አካላትን አቅምና ድጋፍ ዓነቶች መለየት<br><br>2.ለሚደረጉ ትብብሮች የሚረዳ የትብብር ስርዓት ማዘጋጀት<br><br>3. የመግባቢያ ሰነድ እንደ አጋር አካላቱ ባህሪ ማዘጋጀት | በ6ወር | በመደበኛ በጀት የሚሸፈን | ኢንዱስትሪ ሚንስቴር | ሁለተኛ ደረጃ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ኢኒሺዬቲቭ | መግለጫና ወሰን | የሚጠበቅ ውጤት | ከኢንሺዬቲቡ ጋር ግንኙነት ያላቸው ስትራቴጂክ ጉዳዮች | የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | የሚያስፈልገው ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | አስፈጻሚ አካል | የትኩረት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ለመዘርጋት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈልጓል፡፡<br><br>በትብብር ስርዓቱ ውጤታማ ለመሆን የጋር መግባቢያ ሰነድ ስራውን በአግባቡ ለመምራት የሚያስፈልግ ይሆናል፡፡<br><br>**ውሰን፡**<br><br>የአምራች ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ ይቻል ዘንድ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ በስልጠና፣ በማማከር እንዲሁም ልምድ ልውውጥ በሚደረጉ ድጋፎችን ለማግኘት መንግስታዊ ያልሆኑትን አገራዊና አለማቀፋዊ አጋር አካላት የሚያካተቱ ይናል | 3.በትብብሩ የሚገኙ የድጋፍ አይነቶችን በስራ ላይ ማዋል | | 4.በተዘጋጀው የመግባቢያው ሰነድ ከአጋር አካት ጋር መፈራረም | | | | |

*አባሪ ሁለት፡- የአቅም ልማት የካፒታል ፕሮጀክት*

## *የፕሮጀክቶች የፋይናንስ ፍላጎት*

| ተ.ቁ | ፕሮጀክቶች | የታሰበለት አላማ | የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ኮምፖነንቶች | ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ | የሚጀመረበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተጠየቀ ካፒታል በሚሊዮን ብር | ፕሮጀክቱን የሚያስፈፅም አካል ባለቤት[1] |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የውስጥ አቅም ልማት ፕሮጀክት ወይም የቁርኝት ፕሮጀክት | የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን እና የሁለቱን ተጠሪ ተቋማት የሰው ሃይል አቅም ግንባታና የሁለቱ ተጠሪ ተቋማትን በሙሉ ቁመና መደገፍ የሚያስችል የአሠራርና የሰው ሃይል መፍጠር፤ | 1. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ስልጠና<br>2.የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ስድስቱን ማዕከላት ያላተተ የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ስልጠና<br>3.የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ስልጠና | አዲስ አበባ | 2014 ዓ.ም. | 2022 ዓ.ም | 870 | የኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትንና የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት |
| 2. | የመረጃ አሠራር ዝርጋታና የዕውቀት አስተዳደር ስርዓት ዝርጋታና ትግበራ ፕሮጀክት | የማኑፋክቸሪንግ መረጃን በዘመናዊ መንገድ እንዲደራጅ የሚያደርግ የዘመናዊ ስርዓት ዝርጋታና የዕውቀት ዕቀባ አሠራርን | 1. የማኑፋክቸሪንግ መረጃ ስርዓትን የማሻሻል<br>2. በተጠሪ ተቋማትና በክልልና ከተማ መስተዳድር የመረጃ ስርዓቱን የመዘርጋት ስራ<br>3. የዕውቀት ዕቀባ አሠራርን ከሚ/ር መ/ቤት እስከ ተጠሪ | አ/አ እና በሁሉም ክልልና ከተማ መስተዳድር | 2016 | 2018 | 188 | ኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ ሁለቱ ተጠሪ ተቋማት እና የተመረጡ ክልልና ከተማ አስተዳደር |

[1] የፕሮጀክቱ ባለቤት፡ የመንግስት እና ከመንግስት ውጭ ሲሆን ከመንግስት ውጭ ለምሳሌ፡ በግሉ ዘርፍ፣ በህብረተሰቡ፣ እና ሌሎችም፡፡

| ተ.ቁ | ፕሮጀክቶች | የታሰበለት አላማ | የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ኮምፖነንቶች | ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ | የሚጀመረበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተጠየቀ ካፒታል በሚሊዮን ብር | ፕሮጀክቱን የሚያስፈፅም አካል ባለቤት[1] |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በመዘርጋት የዘርፉን ችግር በዕውቀትና በሳይንሳዊ መንገድ ለመፍታት የሚችል አቅም መፍጠር | ተቋማት በተሟላ አግባብ መዘርጋትና መተግበር | | | | | |
| 3. | የህንፃ ግንባታ | ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ ሶስቱን ማዕከላት ጨምሮ እና የኢትዮጵያ ኢንተርኘራይዝ ልማት ኢንስቲትዩት ለቢሮ ህንፃ ግንባታ ስራ በማከናወን ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር | 1. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የህንፃ ግንባታ<br>2. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የማኑፋክቸሪንግ ቴ/ኢ/ም/ ፣ የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ም/ል/ማ እና የምግብና መጠጥ ም/ል/ማዕከላት የህንፃ ግንባታ<br>3. የኢትዮጵያ ኢንተርኘራይዝ ልማት የቢሮ ህንፃ ግንባታ | አዲስ አበባ | 2016 | 2018 | 5,900 | የኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትንና የኢትዮጵያ ኢንተርኘራይዝ ልማት |

| ተ.ቁ | ፕሮጀክቶች | የታሰበለት አላማ | የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ኮምፖነንቶች | ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ | የሚጀመረበት ጊዜ | የሚጠናቀቅበት ጊዜ | የተጠየቀ ካፒታል በሚሊዮን ብር | ፕሮጀክቱን የሚያስፈፅም አካል ባለቤት[1] |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4. | የተጠሪ ተቋማት የወርክሾፕ፣ የላብራቶሪ ፋሲሊቲ ግንባታና መሣሪያ ማሟላት | የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትና የኢትዮጵያ ኢንተርኘራይዝ ልማት መሪ ተቋም ወይም የልቀት ማዕከላት እንዲሆን በማስቻል በማኑፋክቸሪንግ ዘርፋ የተቀመጡ ራዕይና ተልዕኮ ማሣካት ነው፤ | 1. የአኢልኢ የስድስት ማዕከላት የወርክሾፕ፣ የላብራቶሪ ፋሲሊቲ ግንባታና መሣሪያ ማሟላት<br>2. የኢኢል የወርክሾፕ ግንባታና መሣሪያ ማሟላት | አዲስ አበባ | 2016 | 2018 | 8,600 | የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትንና የኢትዮጵያ ኢንተርኘራይዝ ልማት |